ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D/N Solomon Yohannes

# ሁለተኛ መርሐ ምእመናን ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911660113
0111/271609
D/N Solomon Yohannes

ተኀትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ወ፬ቱ ዓመተ መንግሥቱ
ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ወበኀምስ ዓመተ ሢመተ ሊቀ ጵጵስናሁ ለብፁዕ
አባ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

ከቤተ ክህነት ታሪክና ድርሰት ክፍል ተዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ
ምእመናን ማስጠንቀቂያ እንዲሆን ታተመ ።

አዲስ አበባ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ፡ ም፡

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ቍጥር | መራሕያነ አርእስት ። | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር ። | ፱ |
| ፪ | ስለ ወላዲተ አምላክ አማላጅነት ። | ፳፰ |
| ፫ | ለወላዲተ አምላክ ሰጊድ ስለማቅረብ ። | ፵፬ |
| ፬ | ስለ ጻድቃንና ስለ ሰማዕታት አማላጅነት ። | ፵፮ |
| ፭ | ስለ አክብሮት ስግደት ። | ፶፯ |
| ፮ | ስለ መጽሐፈ ኄኖክ ። | ፷፫ |



ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ፤ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም ።

ይህ መጽሐፍ ፤ የወረት ባህልን የተከተለ ልዩ ልዩ ዘመናዊ አሳብን እየተቃወመ ፤ ከቅዱስ መጽሐፍ ተያይዞ የመጣውን ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ባህል ያሳብል እንጂ ፤ ከቅዱስ መጽሐፍ የራቀ ስሜትን በፍጹም ፤ አልተከተለም ።

የብሉይና የሐዲስ መምራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብሉይን በሐዲስ ተርጉሞ ፤ የሁለቱንም ምሥጢራት አስማምቶ (አገናዝቦ) ስለ ሰጠን ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ብሉይን ጠቅሰው ሐዲስን ፤ ሐዲስን ጠቅሰው መጻሕፍተ ሊቃውንትን እየጠቀሱ ወደ አሁኑ ትውልድ ያስተላለፉት ሥርዓታዊ ባህል ፤ ከብሉያት እስከ መጻሕፍተ ሊቃውንት ድረስ ፤ አንድ አቋም ባለው ትርጓሜ ፤ ወይም ምሥጢር የተያያዘና የተመሠረተ ነው እንጂ ፤ ብሉያትን ከሐዲሳት ፤ ሐዲሳትን ከሊቃውንት የሚለያይና የሚያራርቅ ግብዝነት አልተቀላቀለበትም ።

ስለዚህ ፤ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰማንያ አንዱን መጻሕፍት ቃል ተቀብላ ሥረ ወጥ የኾኑ ንባባቸውንና ትርጓሜያቸውንም አስማምታ ይዛ ኖራለች ።

ምእመናኖቿን የምትመራበት ዶግማ ሥርዓት በዚህ ላይ የታነጸ ሲሆን ፤ አንድ ነቃፊ ሰው ከብሉይና ከሐዲስ ጋራ የተባረሩትን (አዋልድ የተባሉትን) መጻሕፍት መቀበሏን ምክንያት አድርጎ ክብሯን የሚደፍር ንግግር አድርጎዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሊቃውንቶቿ ከሁለት ሺህ ዘመን ፣ በላይ ናላቸውን የትርጓሜ ዓላማ ፤ የምሥጢር ከተማ አድርገው በሊቅነታቸው ያጋነኗትንና ያደመቋዋትን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ክብር መድፈር ከጽድቅ ገብቶ የሚቈጠርለት መስሎት ይሆን?

ልዑል እግዚአብሔር በወዳጆቹ አድሮ ያናገረውን ቃል መቀበል እንዴት ያስነቅፋል ?

ከመጠምጠም መማር ይቅደም እንደ ተባለ ፤ ከመንቀፉ በፊት ሕሊናውን እንዲያቀናለት ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ የብርሃን ዓለም ቅዱስ ጳውሎስን ቃል በተመለከተ ይሻለው ነበር ።

ቅዱስ ጳውሎስ፤ መንፈሳውያን ድርሳናትን መቀበል እንዲገባ ሲያስረዳ፣(አንደኛ)አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፤ ሁላችሁ በተሰበሰባችሁ ጊዜ በቋንቋ የምትጸልዩት መዝሙር ፤ በወንጌልም ለይቶ ያስተማረው(አቡነ ዘበሰማያት)ሊቃውንትም የደረሱት ጸሎት አላችሁ።ሁሉንም በምትጸኑ ግንዘብ ሰውን ለመጥቀም አድርጉ ብሏል ። ፩ኛቆሮ ም ፲፬ ቍ ፳፮ ።

ሁለተኛ) (መንፈስን አታጥፉ) ልባችሁን አታባክኑ ፤ ትንቢትንም አትናቁ፤ ሁሉንም መርምሩ ፤ በጎውን ሥራ ያዙ ብሎ በመንፈሰ እግዚአብሔር የተነገረውን ቃል ሁሉ እንድንቀበል) አዟል ። ፩ ተሰሎ ም ፭ ቍ ፲፱ — ፳፪።



ሦስተኛ) በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈ መጽሐፍ ሁሉ ፣ ፍጹም ትምህርትና ምክር በመሆን ፤ ልቡናን በማቅናት ፣ ጥበብን በመግለጥ ጽድቅን በማሠራት ይጠቅማል ። በእግዚአብሔር ያመነ ሰው በጎውን ምግባር ሁሉ ይማር ዘንድ ብሏል ። ፪ኛ ጢሞ ም ፫ ቍ ፲፮ ።

በዚህ ሐዋርያው በሰጠን ማስጠንቀቂያ፣የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዋልድ (አምግራፋ) የተባሉትን መጻሕፍት በመንፈሰ እግዚአብሔር መደረሳቸውን መርምራ ፤ ደራሲያኖቻቸውም እግዚአብሔር ያደረባቸው መሆናቸውን ዐውቃ ተቀብላቸዋለች ።

ሆኖም ፣ ተቀብላ ከብሉያትና ከሐዲሳት ጋራ አስማምታ ትሠራባቸዋለች መባሉ ስለዚህ ሲሆን ፤ ክብሩዋን ለመድፈር መሞከር የክርስትና ሥርዓት አይደለም ።

ይልቁንም ፣ ሰማንያ አንዱ መጻሕፍተ ሕግ የመንፈስ ቅዱስ ፋና ሆነው የሚያበሩላትን ፤ ሊቃውንቶቿም የብርሃን አዕማድ ሆነው ከሁለት ሺህ ዘመን በላይ የደገፋዋትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በቢላት አነጋገር ለማጥቃት መሞከር በስንደው መካከል ክርዳድን እንደ ዘራው ዐራዊ ወይም እንስሳ ዐራዊ መሆን ነው ።

እንዲሁም ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ልቡን ፣ ኵላሊቱን ፣ አንጀቱን ፣ ገበቱን ገላልጠው የሚያውቋትን የኢትዮጵያን

www.ethiopianorthodox.org

ሊቃውንት አስተያየት፤ከእውነተኛ ምሥጢር በተራቆተ ዘለፋዊ አለንጋ መግረፍ ግሡጽ ትምህርት ከለመሆን የነቃ አንደበራነት ነው ።

የሆነ ሆኖ ፤ መርሐ ምእመናን የተባለ ይህ መጽሐፍ በስድስቱ መራሕያን አናቅጽ የተነገሩትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በህሎች ለማስረዳት ስለ ተዘጋጀ፡ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ፡ ለኦርቶዶክሳዊው መሪዎችን ለግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሙሉ ሕይወትንና ዕድሜን እየለመኑ፤ሊቀ ጳጳሳት ሆነው ተሾመው በመንበረ ማርቆስ ለተቀመጡና አሁን የአምስተኛውን ዓመት በዓል ሢመታቸውን ባርከው ለጀመሩልን ብፁዕ አቡነ ባስልዮስም የተሰጣቸው ሀብት ጸጋና ረድኤተ እግዚአብሔር ለብዙ ዘመናት እንዲሆን እየተማለሉ በመጽሐፉ ፍሬ ነገር እንዲጠቀሙበት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተስፋ ታደርጋለች ።

## ፩ኛ ምዕራፍ ።

### አምልኮተ እግዚአብሔርን በልባችን ውስጥ ስለ ማበርታት

የክርስቲያንን ልብ የማይጠፋ ብርሃን ሆኖ ሁል ጊዜ የሚያበራው አምልኮተ እግዚአብሔር እንደሆነ የታወቀ ነው ።

ማናቸውም ሰው ፤ ከአበው እንደ አብርሃም ፤ እንደ ይስሐቅ ፤ እንደ ያዕቆብ ፤ እንደ ኢዮብ ፤ ከነገሥታት እንደ ዳዊት ፤ እንደ ሕዝቅያስ ፤ እንደ ኢዮስያስ ፤ ስሜቱን ጥልቅ አድርጎ እግዚአብሔርን ከአመለከውና ከወደደው፤ ድንቁርናው በዕውቀት ፤ ማጣቱ በማግኘት ፤ ድካሙ በኃይል እየተለወጠለት መንፈሳዊ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ረድኤት ሲታደስለት ይኖራል ። መዝ ፺፩

የቅጽበተ ዓይን ያህል ስንኳ በማይወላውል ልብ እግዚአብሔርን ከመለከ ፤ ጸሎቱ ያርግለታል ፤ ሥራውም ይበረክለታል ፤ ዘሩም ይበዛለታል መዝ ፻፲፪ ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፤ አምልኮታቸውን (ሃይማኖታቸውን) በማጽናታቸው ከልዑል እግዚአብሔር በረከት ዘርእ ያገኙ የደጋጎቹን አበው የአብርሃምን ፤ የይስሐቅን ፤ የያዕቆብን ፤ የኢዮብን ፤ የጦቢትን ፤ የንጉሠ እስራኤል ዳዊትን ታሪክ ልናስታውስ ይገባል ።

፩ኛ/ ታላቁ ሰው አብርሃም ፤ የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሽማግሌ በሆነ ጊዜ ፤ እነሆ ኪዳኔ ከንተ ጋራ ነው ። ለብዙ

www.ethiopianorthodox.org

አሕዛብም አባት ትሆናለህ ፤ ከዛሬም ወዲያ ስምህ አብ ራም ተብሎ አይጠራ ፤ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ነው ፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌ አቁሜሃለሁና ።

እጅግም አበዛሃለሁ ፤ ለአሕዛብም አባት አደርግሃ ለሁ ። ነገሥታትም ከንተ ይወጣሉ የሚል ቃለ ተስፋ ከልዑል እግዚአብሔር መቀበሉ ሕሊናውን ሳያወላውል እግ ዚአብሔርን በማምለኩ ነው ። ኦሪ፡ ዘፍ፡ ም፡ ፲፯ ቁ ፬-፯ ።

፪ኛ/ ይስሐቅ በችግር ምክንያት ወደ ፍልስጥኤም ንጉሥ ወደ አቤሜሌክ በሔደ ጊዜ ፤ እግዚአብሔር ተገ ልጦ እንዲህ የሚል ቃለ ተስፋ ሰጥቶታል ።

እኔ በምነግርህ ምድር ተቀመጥ እንጂ ፤ ወደ ምስር አትውረድ በዚች ምድር ተቀመጥ ፤ ከንተ ጋራም እሆና ለሁ ፤ እባርክሃለሁም ። ይህችን ምድር ሁሉ ላንተ ፤ ለዘር ህም እሰጣለሁ ፤ ለአባትህ አብርሃምም የማልሁትን መሐላ እፈጽማለሁ ።

ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ ፤ ይህ ችንም ምድር ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ ፤ የምድርም አሕ ዛብ በዘርህ ይባረካሉ ፤ አብርሃም ቃሌን ሰምቷልና ፤ ያዘ ዝሁትንም ትእዛዜን ጠብቋልና ፤ ፍርዴንም ፤ ሕጌንም ጠብቋልና ፤ ኦሪ፡ ዘፍ፡ ም፡ ፳፮ ቁ ፩-፮ ።

ይስሐቅ ተስፋ ሥጋ ፤ ተስፋ ነፍስን የተመላ ይህን ቃለ በረከት ከልዑል እግዚአብሔር ለመቀበል የቻለ ፤ ልዑል እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡናው በማምለኩ ነው ።



፫ኛ/ ያዕቆብ ወደቤቴል ወጥቶ ለእግዚአብሔር መሥ ዋዕት በሠዋ ጊዜ ፤ እግዚአብሔር ተገልጦ እንዲህ ብሎ ታል ።

እኔ ሁሉን የምይገዝ እግዚአብሔር ነኝ ። ለምልም፤ ብዛም ፤ ሕዝብ ፤ አሕዛብ ከንተ ይሆናሉ ፤ ነገሥታትም ከወገብህ ይወጣሉ ። ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠኋትን ምድር ላንተ እሰጣለሁ ።

ከንተ በኋላም ለዘርህ ምድሩን እሰጣለሁ ። ኦሪ፡ ዘፍ፡ ም፡ ፳፰፡ ቁ ፲፩-፲፫ ።

ያዕቆብ ፤ ይህንን ከፍተኛ ቃለ በረከት ከእግዚአብ ሔር መቀበሉ ፤ ቅዱስ መጽሐፍ እንደነገረን ቤተ ሰቦቹ ሌሎችን አማልክት (ጣዖታትን) ከመካከላቸው እንዲያስ ወግዱ እያዘዘ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ማምለክን በፍ ጹም ልቡናው አጽንቶ ስለ ያዘ ነው ።

፬ኛ/ ኢዮብ፤ በልጆቹ ፤ በከብቶቹና በሀብቱ ሁሉ ላይ ብርቱ አደጋ ወድቆ ባዶውን ከአስቀረው በኋላ ፤ ልብሱን ቀዶ ፤ ራሱንም ተላጭቶ ወደ እግዚአብሔር እየሰገደ ፤ ራቁቴን ከእናቴ ሆድ ወጣሁ ፤ ወደ መሬትም ራቁቴን እመለሳለሁ ፤ እግዚአብሔር ሰጠ ፤ እግዚአብሔርም ነሣ ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ብሎ በችግሩ ምክ ንያት ምንም የብስጭት ኃጢአት ሳይሠራና አምልኮተ እግዚአብሔርን ከሕሊናው ሳያናውጥ ቢቈይ ፤ ቸር እግዚ

www.ethiopianorthodox.org

ኢብሔር እስከ መጨረሻ ያደረገውን ትዕግሥቱን ተመልክቶ ፤ የትዕግሥቱንና የእምልክቱን ዋጋ ሰፋ አድርጎ ሰጥቶታል ። በላዩ ልዩ ልዩ አደጋ ከመድረሱ በፊት ሰባት ወንዶች ፤ ሦስት ሴቶች ልጆችና ብዙ ቤተ ሰቦች ነበሩት ። ከከብትም ወገን ሰባት ሽህ በጎች ። ሦስት ሽህ ግመሎች ፤ አምስት መቶ ጽምድ በሬዎች ፤ አምስት መቶም አህዮች ነበሩት ። መጽ ኢዮ ምዕ ፩ ቁ ፪-፬ ።

ኢዮብ ልበ ቅን የሆነ ፤ እግዚአብሔርን የፈራ(የመሰከ) ከክፉ ሥራም የራቀ የሙት ልጅ አሳዳጊ ፤ የተራበ የሚያበላ፤ የታረዘ የሚያለብስ ደግ ሰው ስለሆነ ፤ ሰይጣን በመልካም ሥራውና በእምልክቱ ጽናት ቀንቶ የፈተና ምክንያት እስኪያመጣበት ድረስ ፤ በዚህ በተነገረው ሀብተ ሥጋ አጅግ በልጥጎ ፤ ምንአልባት ልጆቹ እግዚአብሔርን በልባቸው በድለው ይሆናል በማለት ስለልጆቹ መሥዋዕት እየሠዋና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈጸመ በመንፈሳዊ ኑሮ ይኖር ነበር ።

ኋላም ፤ ሰይጣን በመጣበት ፈተና ምክንያት ፤ ሀብተ ሥጋውን ከማጣቱ ቀጥሎ አካሉ ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቍስል (በደዌ ሥጋ) በተያዘ ጊዜ ፤ ሚስቱ፡ መንፈሷ ግብዝ ሆኖበት እምላክኽን ክደ ሙና ሙት ብላ የስንፍና ነገር ብታቀርብለት ፤ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ ፤ ከእግዚአብሔር በጎውን እንደ ተቀበልነ መከራውንስ አንቀበለውምን ?



ብሎ በጭንቅ መከራው ጊዜ ሚስቱ ያቀረበችለትን ብስጭት የተመላበትን ፈተና በትዕግሥት አልፎ በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ ቆሞ ተገኘ እንጂ መንፈሳዊ ኑሮውን አላናወጠም ።

ዛሬም ፤ በሚስቱ ፤ በልጁ ወይም በቤተ ሰቡ ስንፍና ምክንያት ዘመኑ የወለደውን ይዘህ ፤ ከእግዚአብሔር ተለይተህ ኑር የሚል በዓለማዊነት የተሸፈነ የፈተና አነጋገር የሚቀርብለት ማናቸውም ክርስቲያን ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከሕሊናው ሳያናውጥ ፤ ጊዜ ያቀረበለትን ፈተና በፍጹም ትዕግሥት ካለፈ ፤ ኢዮብ በትዕግሥቱ ብዛት ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ጸጋ ለመቀበል ይችላል ።

ኢዮብ አምልኮተ እግዚአብሔርን በማጽናቱ ፤ መከራው እንደመብዛቱ መጠን ፤ ጸጋ ስለበዛለትና የእግዚአብሔር ባለሟል ስለሆነ ፤ በመከራው ጊዜ የስንፍና እንጂ የቅንነት ፤ የሚያበሳጭ እንጂ የሚያስደስት ነገር ያልተናገሩትን ኤልፋዝ ቴማናዊ ፤ በልዳዶስ አውኬናዊ ፤ ሶፋር አሚናዊ የተባሉትን ሦስቱን ወዳጆቹን ፤ እግዚአብሔር ስለኔ እንደ በለሚሉ ፤ እንደ አገልጋዩ እንደ ኢዮብ የቅንነት ነገር ባለመናገራችሁ ቍጣዩ በእናንተ ላይ ስለተኰሰ ፤ ወደአገልጋዩ ወደኢዮብ ሒዱና ስለራሳችሁ የሚቃጠል መሥዋዕት አሳርጉ ፤ አገልጋዩ ኢዮብም ይጸልይላችሁ ብሎዋቸው ነበርና ፤ እንደ አላቸው ቢያደርጉና

www.ethiopianorthodox.org

አምላክ አማልክት በሆነ በታላቁ አምላክ እግዚአብሔር ማመኑን በደስታውም በመከራውም ጊዜ ሳያናውጥ ትዕግሥቱን እስከ ፍጻሜ ቢያደርስ ነው እንጂ ፤ ኃጢአትንና ዐመፃን በመሥራቱ ፤ ወይም ከአምልኮተ እግዚአብሔር በመሳሳቱ የሚያገኘው ገናንነት ለጥቂት ጊዜ ከመሆኑ በቀር ለብዙ ዘመን የሚኖር አይደለም ። የጥቂት ጊዜ ገናናነቱም ትቶለት የሚሔደው እንደ ነዌ ፤ እንደ ኪራም ፤ እንደ ፈርዖን ፤ እንደ ሰናክሬም ፤ ክፉ ጨካኝ ፤ ትዕቢተኛ ፤ ግፈኛ ፤ ዐመፀኛ መባልንና ስዘላለሙ መረገምን ነው ።

፳ኛ ጠቢብ ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከጸና ሰው መንፈሳዊ በረከት የማይርቅ መሆኑን ሲያስረዳ ፤ ለልጁ ስጠብያ ልጅ ስለተቸገርን አትፍራ፤ እግዚአብሔርን ከፈራኸው (ከመለከው) ኃጢአት መሥራትንም ትተህ ከገለገልከው ብዙ በረከት አለህ ብሎ ምክር ሰጥቶታል ። ጠቢ. ፡ምዕ፡ ቍ፳፡ ።

የሆነ ሆኖ፤ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ እንደእነ ኢዮብ በፍጻሜ የሚያገኘው እድሉ እንዲያምርለት በየጊዜው አምልኮተ እግዚአብሔርን ሳይዘነጋ ፤ ሃይማኖቱን ሳያዛባ ልቡን በትዕግሥት ማደስና መቀደስ ይገባዋል ።

ሕሊናው በትዕግሥት መሠረት ላይ ተደላድሎ ከቆመና ከጸናም ፤ የእግዚአብሔር ምሕረቱ ፤ ቸርነቱ በእሱ ላይ መገለጡ አይቀርም ።



ይኸውም በቅዱሳን ነቢያትና በኢዮብ ታሪክ ታውቋል ። ሐዋርያው ያዕቆብ ይህንኑ ሲያስረዳን እንዲህ ብሎናል ።

ወንድሞቻችን ፤ መከራችሁን ለመታገሥ ምሳሌ (አርአያ) የሚሆኗችሁ ለእግዚአብሔር ታዘው ትንቢት የተናገሩ ነቢያት አሉላችሁ ፤ መከራውን የታገሡትንም እነሆ እናመሰግናቸዋለን ።

የኢዮብንም ትዕግሥቱን ሰምታችኋል ፤ እግዚአብሔርም እንደፈጸመለት አይታችኋል ፤ ቸርነቱና ይቅርታው ብዙ ነውና ። ያዕ ም ፭ ቍ ፲-፲፪ ።

ታሪክ ፤ በጥንታዊነት ፤ በማዕከላዊነት ፤ በደኃራዊነትም የሚጓዝበትን መሥመሩን የማይለቅ ስለ ሆነ ፤ ለደጉ ሰው ለኢዮብ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ይቅርታ ያስገኘ ይህ ሀብተ ትዕግሥት ፤ አሁን በኛ ዕድሜ በደጉ ንጉሠ ነገሥት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልቡና አድሮ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ይቅርታ ማስገኘቱን ልናስታውስ ይገባናል ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ እንደ አባታቸው ዳዊትና እንደ ኢዮብ ከሕፃንነታቸው ጀምረው አምልኮተ እግዚአብሔርን አጥብቀው ፤ ጠንቅቀው የያዙ ከመሆናቸው በላይ ፤ ፍቅረ እግዚአብሔር ያደረባቸውና ትዕግሥት የመላባቸው ሙሉ አስተዋይ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሁለቱም ባለታሪኮች በትዕግሥታቸው ብዛት ከእግዚአብሔር ያገኙትን ዋጋ በመመልከት ምንም ትዕግሥትንና ትዕግሥትን ብናነጻጽር ፤ ኢዮብ ፈተና የተቀበለው በልጆቹ ፤ በሚስቱ ፤ በሕይወቱና በግል ሀብቱ (በቤቱ ውስጥ ባለው) ነው ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ፣ ባምስቱ የጠላት ወረራ ጊዜያት ፈተናን የተቀበሉ ከዚህ ብዙ ልዩነት ባላቸው ምክንያቶች ነው ።

ይኸውም ፤ በትዕግሥት ጸንተው ስለ መላው ኢትዮጵያውያን መከራ ብዙ ሕሊናዊ መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር አቅርበዋል ማለት ነው ።

ሆኖም ፤ ኢዮብ ትዕግሥቱን ወደ ፍጻሜ ማድረሱ ዕዕፍ ድርብ ሀብትን እንዳስገኘለትና እንደ ገና በበለጠ ደስታና ክብር ተመልቶ ብዙ ዘመን እንደኖረ ፤ ግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከመደነቅ በላይ ያለውን ትዕግሥታቸውን ወደ መልካም ፍጻሜ ማድረሳቸው ለመላ ኢትዮጵያ የተረፈ ደስታና ክብርን እንዳስገኘላቸው እነሆ እናያለን ።

ይህንንም የማስገኘት እድል የተሰጣቸው የአባታቸው የዳዊት ሀብት ያደረባቸው በመሆናቸው ነው ።

አባታቸው ዳዊት ሕዝቡ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመቈጠራቸው የተነሣ በዐውደ አርና ሠራዊቱን ለማ



ጥፋት የቃጣ መልአከ እግዚአብሔር በሰማይና በምድር መካከል በእጁ ሰይፉን መዞ ቆሞ ፤ የተመዘዘው ሰይፉም ወደእገሩ ኢየሩሳሌም ተዘርግቶ በየ ጊዜ ፣ ከሽማግሌዎቹ ጋራ ማቅ ለብሰ በግንባሩም ወድቆ (ሰግዶ) ስለሕዝቡ ልመናውን ወደእግዚአብሔር ከቀረበ በኋላ ፤ መሥዋዕት ሠውቶ ሕዝቡን በማማለድና ለመዓት የታዘዘው የመልአኩ ሰይፍ እንዲመለስ በማድረግ የርኅራኄ ሥራ ሠርቷል። ፩ መጽ ዜና መዋ፡ም፡ ፳፩ ቁ ፲፮-፲፱ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ፤ በምስቱ ዘመናት ሥቃይ በሕዝባቸው ሕይወት ላይ የወረደውን መራር መከራ እየሰቡ ፤ ሕሊናዊ መሥዋዕታቸውንና እንባዐዊ ጸሎታቸውን ወደ እግዚአብሔር ከማቅረብ አላቋረጡም ነበርና መሥዋዕታቸው ዐርጎ ፤ ጸሎታቸውም ተሰምቶ ፤ እኛን ሕዝቦቻቸውን እንደጠቀመ እነሆ እንመለከታለን ።

ይህ ሁሉ ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከማጽናት የተገኘ በረከታዊ ፍሬ ነው ።

አምልኮተ እግዚአብሔር ኃይለ ሥጋን የሚያረታ ፤ ኃይለ ነፍስን የሚያበረታ ስለሆነ፤ ወደእሱ አምዐነት፡ ወደ እሱ መጠጊያነት የተጠጉ ሁሉ ምንጊዜም አላፈሩም ።

በአርእስቱ ጀምረን እየተትነው እንደመጣን ፤ አምልኮተ እግዚአብሔር ፤ቡሩክ ዘርን ፤ ቡሩክ ሀብትን ፤ቡሩክ

www.ethiopianorthodox.org

ዘመንን የሚያስጥ ሲሆን ፤ ከእሱ ወጥቶ ወደአምልኮ ባዕድ መሔድ ራስን እንደ ማታለል ፤ ወይም እንደ መግደል የሚቈጠር ነው ።

ለልቡናችን፤ ለሕይወታችን ብርሃን የሆነውን አምልኮተ እግዚአብሔርን ትተን ሕሊናችንን ከባድ ጨለማ ወደ ሆነው አምልኮ ባዕድ (አምልኮ ጣዖት) ያዘነበልን እንደሆነ ቡሩክ ዘርን ቡሩክ ሀብትን ቡሩክ ዘመንን ማግኘታችን ይቅርና ከአብራካችን የወጡ ልጆቻችን ፤ ወይም ቤተ ሰቦቻችን በጠላትነት ተነሥተውብን ሕይወታችንን እስከማጥፋት እንዲደርሱ በሰናክሬም አጠፋፍ ልንረዳ እንችላለን ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፤ የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ ፤ የፋርስ ንጉሥ ሰናክሬም የዕብራውያንን ንጉሥ ሕዝቅያስን ለመውጋት ወደኢየሩሳሌም ዘምቶ ሳለ ፤ መልአከ እግዚአብሔር መቶ ሰማንያ አምስት ሽህ ሠራዊት በገደለበት ጊዜ ፤ ወደከተማው ወደነነዌ ተመልሶ ለጣዖቱ ሲሰግድ ፤ ሰርሰር ፤ አድራ ማሌክ የተባሉ ልጆቹ በሰይፍ መትተው እንደገደሉት ይነግረናል ። ትንቢ፡ ኢሳ፡ ም፡ ፴፯ ቁ ፴፮-፴፰ ።

እግዚአብሔርን ማምለክ ትቶ ፤ ፍጡርን ማምለክና ለፍጡር የአምልኮት ስግደት መስጠት እንደዚህ ያለ መቅሠፍት የሚያመጣ ስለሆነ ፤



ዘሬም ፤ ማናቸውም ሰው የሰናክሬም ጕስቍልና እንዳይደርስበት ይጠንቀቅ ።

ልዑል እግዚአብሔር የማያደርገውን አይናገርም ፤ የተናገረውንም አያስቀርምና ፤ መጀመሪያ ለሙሴ ዐሥሩን ሕገጋት ሲሰጥ ፤ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክትን አታምልክ ከለው ቀጥሎ የአምላክህን እግዚአብሔርን ስም ከንቱ አታድርግ ፤ እግዚአብሔር ስሙን ከንቱ ያደረገውን ሳይቀሥፈው አይተወውምና ብሏል። ኦሪ ፡ ዘፀ ፡ ም፡ ፳፡ ቁ ፯ ።

ይህን የእግዚአብሔርን ቃል ከሰማወስን ዘንድ ፤ ሰናክሬም እንዴት ብሎ የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ አድርጎ ነበር ? ብለን እንመርምር ። ሰናክሬም ፤ ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ከጠላታችን ከሰናክሬም ያድነናል ብሎ አምልኮተ እግዚአብሔርን ማድናቱን ተመልክቶ ፤ እንዲህ እያለ የድፍረትና የትዕቢት ነገር ተናግሮ ነበር ።

ሕዝቅያስ፡ እግዚአብሔር ያድነናል እያለ አያባብላችሁ ። በውኑ የአሕዛብ አማልክት ምድራቸውን ከአሶራውያን ንጉሥ እጅ አዳኑን ? የሐማትና የአርፋት አማልክት የትአሉ ? የሰፋሩሄምስ አማልክት የት አሉ ? በውኑ ሰማርያን ከእጄ አዳኑ ? ማነው ከዚች ምድር አማልክት ሁሉ ምድሩን ከእጄ ያዳነ ? እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከእጄ ያድን ዘንድ።ትንቢ፡ኢሳ፡ም፡፴፮፡ቁ ፲፰-፳፩፤

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በላይ የተነገረው ታሪክ እንደ አስረዳን፤ ሰናክሬም የአምላክህን እግዚአብሔርን ስም ከንቱ አታድርግ የተባለውን መጽሐፋዊ ሕግ ተላልፎና የእግዚአብሔርን አምላክነት ከጣዖታት እንዳንዱ አስመስሎ የድፍረት ነገር በመናገሩ በእግዚአብሔር ኃይል ተቀሥፎ ሞቷል ።

የሆን ሆኖ ፤ ይህ የመቅሠፍት ፍርድ እንደ ሰናክሬም የእግዚአብሔርን ስም በሚያቃልሉና የአምልኮትን ስግደት ለፍጡራን በሚሰጡ ሁሉ ላይ ሲፈጸም ይኖራል ።

በዚህም ታሪክ ላይ ፤ በመከራው ጊዜ ወደእግዚአብሔር የተማጠነ እንዲድን በሕዝቅያስ ፤ ወደጣዖት የተማጠነ እንዲጠፋ በሰናክሬም ስለተረዳን ፤ የሕዝቅያስ ትሕትና ለተጠቂዎች መነሻ ፤ የሰናክሬም ትዕቢት ለአጥቂዎች መውደቂያ መሆኑ በየልባችን ይታሰባል ።

ይህንኑም በዘመናዊ ሁኔታ ለመረዳት ፤ ሕዝቅያስ ጠላቱ ሰናክሬም ፤ አገሩ ኢየሩሳሌምን በዐመፃ በግፍዕ ሊያጠፋበት በተነሣ ጊዜ ፤ ልብሱን ቀዶ ፤ ማቅም ለብሶ ፤ ወደቤተ እግዚአብሔር ገብቶ ጸልዮ (ምህላ አድርሶ) በትሕትና ወድቆ ተነሥቶ ፤ አገሩ ኢየሩሳሌም የምትድንበትን ምሕረት እንዳስገኘ፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ ፋሽሽታዊ ጠላት በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. አገራቸው ኢትዮጵያን በዐመፃ በግፍዕ ሊያጠፋባቸው በተነሣ ጊዜ ፤ እግዚአብሔር ያድናል ማለትን ከሕሊናቸው ሳይለዩና ከመከራው ከባድነት የተነሣ



ከመንፈሳዊ ተሰፍዎ ላይ መንፈሳቸውን ሳያናውጡ፤ በየገዳማቱና በየአድባራቱ ያስደረሱት ጸሎተ ምህላ ከልዑል እግዚአብሔር ምሕረትን ፤ ቸርነትን አስገኝቶላቸው መነሣት ለግርማዊነታቸው ፤ መውደቅ ለጠላታቸው መሆኑን መመልከት በቂ ነው ።

ሆኖም ፤ አምልኮተ እግዚአብሔር ለተጠቂዎችና ለተገፊዎች ኃይል ሆኖ መኖሩ በየታሪኩ ምዕራፍ ስለታወቀ ፤ የዛሬውና የመጪው ጊዜ ትውልድ ሁሉ ከሌላው ከሥጋዊው ተግባሩ አስቀድሞ ፤ ሁሉን ማድረግ የሚችል ሕሊና አስቦ የማይደርስበት ፤ ሁሉን የፈጠረ ፤ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው (ለዘለዓለም የሚኖር) በአካል በስም በግብር ሦስት ፤ በባሕርይ በፈቃድ በመለኮት አንድ ሆኖ የሚመለክ አንድ አምላክ እግዚአብሔር መኖሩን በልቡና በመምህር ፤ በመጽሐፍ መርምሮ መረዳት ይገባዋል ።

እንዲሁም ፤ በመስጠት ፤ በመንሣት ፤ በመፍጠር ፤ በማሳለፍ በመግዛት አንድ አምላክ መሆኑን አምኖ ዓለማዊ ፈተና እንዳይጥለው ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከተደገፈ መንፈሳዊ ኃይል ከቶ አይለየውም ።

ለእግዚአብሔር ሕሊናዊ ምስጋና ይግባውና ፤ ኢትዮጵያ፤ መፍጠር ፤ ማሳለፍ መስጠት ፤ መንሣት ፤ መግዛት በጠቅላላው ሁሉን ማድረግ የሚቻለው አንድ አምላክ እግዚአብሔር መኖሩን ተረድታ በአምልኮተ እግዚአብ

www.ethiopianorthodox.org

ሔር ደጋፊነት መንፈሳዊ ኃይልን እየለበሰች በየጊዜው የገጠማትን ዓለማዊ ፈተና ስታሸንፍ የኖረችበት ዘመን ከሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስሳ በላይ ሆኗል ።

ኢትዮጵያ ፤ እንዲህ ብዙ ዘመናት በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንታ ፤ በኃይለ እግዚአብሔር ታጥራ ተቀጽራ የኖረች ቅድስት አገር ስትሆን ፤ ታሪኳን ያልተመለከተ አንድ ሰው ፤ አገሬ ኢትዮጵያ ሆይ ፤ አምላኮችህ እንደ አውራጃህና እንደ መንገድህ ብዙዎች ናቸው ብሎ ኢትዮጵያ ጣዖታትን እንደምታመልክ በማስመሰል ተሳድቧል ።

እንዲህ ደፍሮ መሳደቡ ሰይጣን ምትሐቱን አቀሞት እንደሆነ ነው እንጂ ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ፅንጨት ጠርበ ደንጊያ አለዝበ (ጣዖትን ቀርጾ) በማይሰማ ፤ በማይናገር ፍጡር የሚያመልክ ሰው መኖሩን በጆሮዎችን አልሰማንም ፤ በዓይናችንም አላየንም ።

ተሳዳቢው ይህ ብቻ አልበቃ ብሎት ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ቃሉ (ብፁዓን መሐርያን እስመ ሎሙ ይምሕርዎሙ) የሚራሩ ብፁዓን ናቸው እርሳቸው ምሕረትን ያገኛሉና ብሎ የሰጣቸውን ብፅዓን በሚገባ የተቀበሉ አባቶቻችን ሐዋርያትን ፤ ጻድቃንን ሰማዕታትን ጨካኞች ናቸው ፤ ለመዓት እንጂ ለምሕረት ወደእግዚአብሔር አያመለክቱም (አያማልዱም) እያለ ነቅፎዋቸዋል ።



ሰማያዊ ክብራቸውንም እየደፈረ በቧልት የተመላ ሐተታ አድርጓል ።

ይልቁንም በነፍስ ሕይወት ሕያዋን መሆናቸውን በውቀን የምናቀርብላቸውን የአክብሮት ስግደት ምክን ያት አድርጎ ያለ እግዚአብሔር ሌላ አምላክ አለ ብለህ አታምልክ የሚለውን ሕግ ተላልፋችሁ ፍጡራን የሆኑ ሐዋርያትን ጻድቃንን ሰማዕታትን አምልካችኋል ብሎ ወቅሷል ።

ይህን ድፍረት ስንመለከተው ፤ ሃይማኖተ አሪትን በንግሥተ አዜብ ፤ ሃይማኖተ ወንጌልን በሕጽዋ ለሕንደኬ (በራሷ ተወላጆች መሪነት) ከመቀበሏ በቀር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንዳች ጣዖታዊ ምልክት ያልተገኘባትን ኢትዮጵያን እንዲህ አድርጎ ታሪኳን ለማስተባበል መጣር በምቀኝነት ከተመረዘ መንፈስ የነቃ ይመስላል ።

በእውነቱ እንደእነ ኤልያስ እንደእነ ዳዊት ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናኢዎች የሆኑ ነገሥታት እነንግሥተ አዜብ ፤ እነ አፄ ካሌብ ፤ እነ አፄ ገብረ መስቀል፡ እነአፄ ላሊበላ፤ እነ አፄ ይኩኖ አምላክ፤ እነ አፄ ይስሐቅ፡ እነ አፄ ዘርአ ያዕቆብ፤እነ አፄ ናዖድ፡እነአፄ ሠርፀ ድንግል፡ እነ አፄ ፋሲልና የመሳሰሉት ደጋግ ነገሥታት የነገሡባትን፡ አሁንም ቃላቂ መንፈሳዊ መሪ ግርማዊ ጃንሆይ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለቅብዐ መንግሥት ተመርጠው በፍጹም ክርስቲያናዊ ዕውቀትና

www.ethiopianorthodox.org

አያያዝ የሚመሩዋትን ኢትዮጵያን ፡ ከሊቃውንት ወገንም መተርጕማን ማእምራን የሆኑ እነ እንበረም ፤ እነ ቅዱስ ያሬድ እነ አባ ጊዮርጊስ እነአቡነ ዜና ማርቆስ እነአቡነ ተክለ ሃይማኖት እነአቡነ ቀውስጦስ ፡ እነ አባ ኤልያስ (ወልደ እኅቱ ለአጼ ዘርአ ያዕቆብና) እነዚህን የመሳሰሉት በብቃታቸውና በደግነታቸው የታወቁ ትጉሳን መምህራን፤ የተበጠረ የሠመረ የወንጌልን ቅንጣት የዘሩባትን ኢትዮጵያን የእግዚአብሔር ወዳጆች ፤ ባለሟሎች የሆኑ ሐዋርያትን ጻድቃንን ፤ ሰማዕታትን ማክበርን ምክንያት በማድረግ ፤ በፍቅረ ጣዖት የተነደፉ እስመከሉ ማሙራት ከዲያብሎስ ስሕተት የተባበረ ሐሰት ፤ ከፋሽሽት ወራሪነት ያላነሰ ጠላትነት ነው ።

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን ለኢትዮጵያ ላስነሣላት ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ፤ ዛሬ የግርማዊነታቸው የመገሥገሥ ተራ በደረሳቸው የወዳጆች አገሮች ሁሉ የቀድሞ ታሪኳን ከዘገቡት ከፍተኞች ሰዎች የሚሰማው ጥንታዊትክርስቲያን የመሆኗ ዝና ሲሆን ፡ ጥሩውን ታሪኳን ለማደፍረስ መሞከር ከንቱ ድካም ከመሆኑ በላይ ፡ ተሳዳቢውን ከኢትዮጵያ በረከት የሚያርቀው ይሆናል ። ቢሆንም ፤ አንዲት አፈር የዐባይን ወኃ ልታደፈርሰው እንዳትችል ያንድ ፡ ሰው ሽሙጥና ለግጥ ሦስት ሺህ ዘመን ያህል በጥራት የተቀመጠውን የኢትዮጵያን ታሪክ ሊያደፈርሰው አይችልም ።



የሬት ጠብታም በጋን ውስጥ ያለውን ወይን ልታመረው እንዳትችል ፡ በስድቡ ጠብታ ጣፋጩን የኢትዮጵያን ታሪክ መራራ ሊያደርገው አይችልም ።

ስለሆነም ፤ የኢትዮጵያ ምእመናን ራሳቸውን ፤ ልጆቻቸውን፤የልጅ ልጆቻቸውን ስድብን ከሚያስተምሩ ከተን ኰለኞች ስሕተት እንዲጠብቁ የምናሳስባቸው ይህን የሐዋርያውን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር ነው ።

(አስተብቋዕኩከ ከመ ትገሥጾሙ ከመ ኢያምጽኡ ካልአ ትምህርተ ወኢያምጽኡ መሐደምተ ፡ ወዘውዐ ነገር ፡ ዘይፈጥሩ በዘያስሕቱ ፤ ወያመጽኡ ተኃሥሦ ፡ ወየኀድጉ ሕገ እግዚአብሔር ዘበሃይማኖት ።

ወማኅለቅቱሰ ለትእዛዝ ተፋቅሮ በንጹሕ ልብ ፡ ወበሠናይ ግዕዝ ፡ ወሃይማኖት ዘአልቦ ኑፋቄ፡እስመ ቦ እለ አውከኩ ወገብኡ ውስተ ነገር ከንቱ።ወእንዘ ይፈቅዱ መምህራነ ይኩኑ ኢየአምሩ ዘለሊሆሙ ይነቡ ፩ ጢሞ ም ፩ ቍ ፬ - ፯ ።

ሌላ ትምህርትን እንዳያመጡ ትገሥጻቸው ዘንድ ማልድኩህ ። ሰውን ያስቱ ዘንድ ፈጥረው የሚናገሩትን ተረትና ጨዋታ እንዳያመጡ ። የታመነ የእግዚአብሔርን ሕግ ትተው ክርክርን ያመጣሉና ።

የትእዛዝ ፍጻሜ ግን በቀና ልብ መፋቀር ነው ። በበጎ ሥራ ፤ ጥርጥር በሌለበትም ሃይማኖት መጽናት ነው ። ከዚህ ወጥተው ወደከንቱ ነገር የገቡ አሉና ።

www.ethiopianorthodox.org

መምህራንም ሊሆኑ ሲወዱ የሚናገሩትን አያውቁም ።

ይህንን የሐዋርያውን ቃል ከሰማን በኋላ ፤ የንግግራችን መግቻ የምናደርገው ፤ ከልዑል እግዚአብሔር አስተዋይ ዓይን ልቡና የተሰጠው እውነተኛ ክርስቲያን ቀናውን መንገድ ከጠማማው ለይቶ ያስተውል ማለትን ነው ።

በዚሁም ላይ (አምላክነሰ ኃይልነ ፤ አምላክነሰ ፀወንነ። አምላከ አሕዛብ ሰብነ ፤ ወዕፀ ኪነት ኢኮነ) ፈጣሪያችን ኃይላችንና መጠጊያችን ነው ።

አሕዛብ እንደ ሚያመልኩት ድንጊያና በብልኀት እንደሠሩት ዕንጨት አይደለም እያለች በተመሥጦ ወደ እግዚአብሔር ምስጋና ስታቀርብ የኖረች ኢትዮጵያን የሰደበትን መናፍቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን የታሪክ በሎታቸውን ይዘው ሊከላከሉት ይገባል ።

## ፪ኛ ምዕራፍ ።

## ስለ ወላዲተ አምላክ አማላጅነት ።

ቅድስት ድንግል ማርያም ፤ የቃል ኪዳን መሠረትና የተስፋችን ምክንያት ፤ የድኅነታችንም ምልክት የሆነች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከረገ በኋላ ብቻ አይደለም ።

አዳምና ሔዋን፣ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር የወሰነላቸውን ትእዛዝ ተላልፈው የለበሱትን ጸጋ በተገፈፉ ጊዜ፤ በኃጢአታቸው ስለ ተጸጸቱ ፤ በፈታሒነቱ አንጻር መሐ



ሪነቱ ያልተለየ ቸር እግዚአብሔር ፤ ንስሓቸውን ተመልክቶ የምሕረት ቃሉን በሠርክ ስለአሰማቸውና በየጊዜው የሥጋዌውን ነገር (ከቅድስት ድንግል መወለዱን) ስለአናገረ ለሰው ዘር ሁሉ የተሰጠ ቃል ኪዳን ፤ ተስፋ ፤ ድኅነት በእርሷ ላይ እየተመሠረተ መምጣቱ የታወቀ ነው ። ይኸውም በነቢያት ቃል እንደተገለጠ መጻሕፍተ ሐዲሳት ይመሰክራሉ ። ይህንኑም ለማስረዳት ከነቢያት አንዱ ኢሳይያስ ፤ ስለ ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክ ክብር የተናገረውን ትንቢት ልናስታውስ ይገባናል ።

ኢሳይያስ ፤ የሥጋዌ ምሥጢርና የእመቤታችን ክብር በሰፊው ስለተገለጠለት ፤ (ትወፅእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ፤ ወየዐርግ ጽጌ እምጕንዱ) በትር ከዕሤይ ሥር ትወጣለች ፤ ጫፍም ከሥሩ ይበቅላል ብሎ ትንቢት ተናግሮዋል። ኢሳ ም ፲፩ ቍ ፩ ።

በዚህም በነቢዩ በኢሳይያስ ቃለ ትንቢት ፤ በትር የተባለች እመቤታችን ፤ ጽጌ የተባለ ልጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ነው ።

በበትር የወደቀ እንዲነሣበት ፤ የደከመ እንዲጸናናበት ፤ የዛለ ፤ የተሰናከለ እሷን ምርኩዝ አድርጎ እንዲንቀሳቀስባት ፤ በእመቤታችንም ፤ በኃጢአት የወደቀ በፍዳ

www.ethiopianorthodox.org

የተሰናከለ ፤ የሰው ዘር ጽንዐ ነፍስን አግኝቶ ተነሥቶበታልና ምሳሌው ከምሥጢሩ ጋር የተባበረ ሆኗል ።

እኛም ፡ በኃጢአት ስንወድቅ ፤ በፍዳ ስንሰናከል (በጠቀላላው የምግባር ሰባሪዎች ስንሆን) ንስሓችንን አስቀድመን አማላጅነቷን የሕሊናችን ምርጕዝ በማድረግ ከወደቅንበት እንድንነሣበት ይኸው የኢሳይያስ ቃለ ምሳሌ ያስረዳናል ።

የታወቁት የኢትዮጵያ ጻድቅና ሐዋርያ አቡነ ዜና ማርቆስ ፡ የብሉይንና የሐዲስን ምሥጢራት ጠንቅቀው ያውቁ ነበሩና ፡ ቀድሞ በአይሁዳዊነት ግብር ይኖሩ ለነበሩት አባ ጽጌ ብርሃን ኢሳይያስ ተወልእ በትር እምሥርወ ዕሤይ ፤ ወየዐርግ ጸጌ እምጕንዱ ፡ ብሎ የተናገረውን ይህንኑ ትንቢታዊ ቃል በትር የተባለች ድንግል ማርያም ናት ፡ ጽጌ የተባለው ልጅዋ ክርስቶስ ነው እያሉ ቢያስረዷቸው አባ ጽጌ ብርሃን በአይሁዳዊነት ሳሉ የብሉያት መጻሕፍትን የተማሩ ስለነበሩ ምሥጢሩ በቶሎ ገብቷቸው (ሠናየ ተርጐምከ ለትንቢተ ኢሳይያስ) የኢሳይያስን ትንቢት መልካም አድርገህ ተረጐምኸው ብለው አድንቀው ወደ ሃይማኖታቸው ገብተዋል ።

በዚህ ጊዜ ፡ አቡነ ዜና ማርቆስ አጥምቀው ፡ የክርስትና ስማቸውንም ጽጌ ብርሃን ብለው ሰይመው የሐዲሳት



መጻሕፍትንም አስተምረው ሊቀ ካህናት እስከመሆን አድርሰዋቸዋል ።

እኚህም አባ ጽጌ ብርሃን ፡ በወላዲተ አምላክ አማላጅነት ተመሥጠው ማኅሌተ ጽጌን የደረሱ ናቸው ።

አባቶቻችን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ፡ ብሉይን ከሐዲስ ጋር ማነጻጸርና ሐዋርያት ሰብዓ አርድእት ፡ ብዙዎችም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደ ተረጐሙት አድርጎ ማስረዳት ልማዳቸው ስለሆነ ፡ በትር የተባለች ድንግል ማርያም ናት ፡ ጽጌ የተባለ ልጅዋ ክርስቶስ ነው ማለትን የደረሩ ከመጻሕፍተ ሐዲሳት አግኝተው ነው እንጂ ከልባቸው አንቅተው አይደለም ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ የጻፈው ግብረ ሐዋርያት የተባለው መጽሐፍ እንዲህ ይላል ።

(ወእምድኅሬሁ አንገሦ ሎሙ ዳዊትሃ ወሰማዕትከኖ ፡ ወይቤ ረከብክዎ ለዳዊት ወልደ ዕሤይ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ ዘይገብር ኵሎ ፈቃድየ ። ወእምዘርአ ዚአሁ አምጽአ ሎሙ እግዚአብሔር መድኃኔተ ለእስራኤል ኢየሱስሃ በከመ አሰፈዎሙ ግብ ሐ ም ፲፫ ቍ ፳፪–፳፬ ። )

www.ethiopianorthodox.org

ሳኦልን ከሻረው በኋላ ዳዊትን አነገሠላቸው እን ደልቤም የኾነ ሰው ፤ ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ ፤ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ ብሎ መሠከረለት ።

እግዚአብሔርም እንደተስፋው ከዘሩ ለእስራኤል መድኀኒት አድርጎ ኢየሱስን አስነሣ ።

በዚህ በሐዲሳዊው ቃል ዘሩ የተባለች ድንግል ማርያም ፤ መድኀኒት የተባለ ልጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ፤ ይህንኑ በግብረ ሐዋርያት ተጽፎ የሚገኘውን በጉባኤ አትቶ የተናገረው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፤ በኢሳይያስ ቃል በትር የተባለች ድንግል ማርያም ፤ጽጌ የተባለ ልጅዋ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ገልጦ ተናግሮታል ለማለት ይቻላል ።

የምሥጢር ሀብት ተሚልቶ የተሰጠው የኢትዮጵያ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ይህንኑ በመጽሐፈ ኢሳይያስና በግብረ ሐዋርያት ስለ ጌታችንና ስለእመቤታችን የተነገረውን ቃል መሠረት አድርጎ እንዲህ ብሏል ።

ትወፅእ በትር እም ሥርወ ዕሤይ ፤ ወየዐርግ ጽጌ ። ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ ።

ወጽጌ ዘወፅአ እምኔሃ አምሳሉ ለወልድ ። ኅደረ ላዕሌሃ ቃል ሥጋ ኮነ ፤ ወተወልደ እምኔሃ ።

ቅዱስ ያሬድ በሀብተ ትርጓሜ ላይ ሀብተ ምሥጢር የተሰጠው ስለኾነ ፤ እንዲህ አጕልቶ አስረድቷል ።



ሊቁ ሰዊርስም በሃይማኖተ አበው (ወአስተርአየ ለነ በትር እምሥርወ ዕሤይ ። እስመ ዝንቱ በትር ይሜህ ረነ ልደተ ዘኮነ እምድንግል ቅድስት ወንጽሕት ወላዲተ አምላክ ማርያም ዘትሄሉ ዘእንበለ ድንግል በኵሉ መዋዕል ፤ ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ ወዘእንበለ ሩካቤ ፤ ወኢተድ ምርተ ተዋስቦ እስመ በትር ኢይወጽእ ዘእንበለ ዳእሙ በሀላዊ ሥርው ። ወይእዜ ቀዳማዊ እግዚአብሔር ቃል ኃይሉ ለአብ ለሊሁ ጸለላ ለድንግል ።)

## ት ር ጓ ሜ ።

ከዕሤይ ሥር በትር ተገለጠልን ። ይህ በትር ሁልጊዜ ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን አምላክን ከወለደች ከድንግል ማርያም ያለ ዘርአብእሲና ያለሩካቤ ፤ ለመጋበትም ባለ መገናኘት ተደረገውን መወለድ ያስተምረናልና ፤ ሥር ከሌለም በትር ሊወጣ ፈጽሞ አይችልምና ። ዛሬም የአብ ኃይሉ ቀዳማዊ እግዚአብሔር ቃል እርሱ ራሱ በድንግል አደረ (ጋረዳት) ብሏል ።

እንዲሁም የሶርያ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ፤ በድርሰቱ ውስጥ የማትጠፋ ፋና ፤ የማትፈርስ መቅደስ ፤ የቅዱሳን መጠጊያ የሆነች የማትዘነበል የሃይማኖት በትር ነች ብሎ ወድሷታል ።

በዚህ መጽሐፋዊ ማስረጃ ፤ በትር አካላቸው ለተሰበረባቸው ለምእመናን ድጋፍ እንደሆነች ድንግል ማርያም

www.ethiopianorthodox.org

ምግባራቸው ለተሰበረባቸው ሰዎች ድጋፍ መሆኗ ሊታመን የሚገባ ነው ።

አንድ ሰው ፡ ማርያም ድንግል ርኅርኅትና ንጽሕት ፡ ጻድቅትና ቅድስት ናትና ። ክፉም አትወድምና ለኃጥአን አታማልድም ማለቱ ይሰማል ።

ይህ በፍጹም መሳሳት ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርቶስ መከራ በተቀበለ ጊዜ ፡ ለጠላቶቻችን እንድንጸልይ ለእኛ ትምህርትን ሲሰጠን (አባ ኅድግ ሎሙ እስመ በዘ ኢየአምሩ ይገብሩ) አባቴ ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው እያለ ሃይማኖትም ምግባርም ለተሰበረባቸው ፡ በንስሓም ላልፈለጉት ጠላቶቹ አይሁድ እንደ ጸለየላቸው ፤ በዚህም ጸሎቱ አርባ ዘመን ያህል የንስሓ ዕድሜ እንደተሰጣቸው ከቶ አላስተዋለምን ? ሉቃ ም ፳፫ ቍ ፴፬ ።

ጌታችን መሪያችን እንዲህ አድርጎ ለጠላት መጸለይን ያመለከተ ሲሆን ፡ ከልዑል እግዚአብሔር የአማላጅነት መብት የተሰጣት ቅድስት ድንግል ማርያም ፤ ምግባራቸው እንጂ ሃይማኖታቸው ያልተሰበረባቸው ኃጥአን በንስሓ ወድቀው አማልጅን እያሉ በጸለዩ ጊዜ ፡ ታማልዳቸውም እንዴት ይባላል ?



የሰማዕትነት ጀማሪ ቅዱስ እስጢፋኖስም ፤ የጌታውን ቃል ተከትሎ ወንጌልን በማስተማሩ የቀኑ ቤተ አይሁድ በደንጊያ በወገሩት ጊዜ ፡ በጕልበቱ ተንበርክኮ (እግዚኦ ሥረይ ሎሙ ዘንተ ኃጢአቶሙ ፤ ወኢትረሲ በሙ ጌጋየ) አቤቱ ይህችን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ቃል እየጮኸ ሃይማኖትም ፤ ምግባርም ለጐደለባቸው ጠላቶቹ ይጸልይላቸው ነበር ። ግብ ሐዋ ም ፯ ቍ ፷ ።

ቅዱስ እስጢፋኖስ፡ሃይማኖት ለሌላቸው እንዲህ ብሎ የጸለየ ሲሆን ፤ ቅድስት ድንግል ወላዲተ አምላክ ፤ ሃይማኖት ሳይጐድልባቸው ምግባር ለጐደለባቸው ኃጥአን ታማልዳለች ቢባል ፤ እንዴት ነውር መስሎ ይታያል ?

ይህም ሰው ለኃጥአን መራራትና ማማለድ ነውር መስሎ ስለታየው ፡ ማርያም ድንግል ርኅርኅትና ንጽሕት ጻድቅትና ቅድስት ናትና ክፉ አትወድም በማለት ፋንታ ለኃጥአን ታማልዳለች ብለው ጽፈውብታል ብሏል ።

ክፉ ሥራ ሠሩና እኔ አማልዳችኋለሁ የሚል አማላጅ ፡ ስንኳን በመንፈሳዊው በሥጋዊው በኩል እንደሌለ የታወቀ ሲሆን ፤ ንጽሕተ ንጹሐን ፡ ቅድስተ ቅዱሳን ፡ ቡርክተ ቡሩካን የሆነች እመቤታችንን ማማለዷን ክፉን እንደ መውደድ አስመስሎ ክፉ አትወድም በማለት ፈንታ

www.ethiopianorthodox.org



ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ ። ሉቃ
ም ፩ ቊ ፵፰ ።



ለኃጢአተኞች ታማልዳለች አሏት በማለት እውነትን ከሐሰት ጋር ማጋጨት አይገባም ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ፈሪሳውያን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋሬ ተቀምጦ ሲበላ አይተው ፤ ደቀ መዛሙርቱን መምሬችሁ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋሬ ለምን ይበላል ? ሲሏቸው ሰምቶ (ኢመጻእኩ እጸውዕ ጻድቃነ አላ ኃጥአነ ለንስሓ) ኃጥአንን ወደንስሓ ልጠሬ እንጂ ፤ ጻድቃንን ለመጥሬት አልመጣሁም ብሏል ። ማቴም ፱ ቊ ፲፫ ።

መፍቀሬ ንስሓ የሆነ አምላክ ኃጥአንን ወደ ንስሐ ልጠሬቸው መጣሁ ማለቱ ክፋውን ይወዳል ያሰኘዋልን ?

እንዲህ ማለቱ ፤ ክፋን ይወዳል እንዳላሰኘው መፍቀሬት ንስሓ የኾነች እመቤታችን ተነሳሕያን የሆኑ ኃጥአንን አማልዳ ወደእግዚአብሔር ቸርነት ታደርሳለች መባሏ ክፋውን ትወዳለች ተብለች አያሰኛትም ።

እኛ ግን ፡ የተሳዳቢውን መንፈስ ሳንከተል በአማላጅነቷ እየተማጠን ንግሥት ፡ ንጽሕት ፤ ቡርክት ፤ ብፅዕት ምእልተ ጸጋ ፤ ምልእተ ክብር እያልን እንደደጋጉ ሊቃውንት እንደ ቅዱስ ኤፍሬም ፡ እንደ አባ ሕርያቆስ ፡ እንደ ቅዱስ ያሬድ ኢትዮጵያዊ እንወድሳታለን እንጂ ክብሯን አንጠራጠርም ።

www.ethiopianorthodox.org

ውዳሴዋም ከመጻሕፍት ቃል ጋር የተየያዘ መሆኑን ቀጥለን እናስረዳለን ።

፩ኛ/ ንግሥትነ፤ እግዝእትነ እያልን የምንወድሳት ። አባቷ ዳዊት (ወትቀውም ንግሥት በየማንከ ፡ በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ፡ ወኁብርት) ንግሥትም የኦፊርን ወርቅ ለብሳ በቀኝህ ትቆማለች ብሎ የተናገረላትን ትንቢትና መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል (ኢትፍርሂ ማርያም እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር ። ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ፡ ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ። ውእቱ ዐቢየ ወይሰመይ ወልደ እግዚአብሔር ልዑል ፤ ወይሁብ እግዚአብሔር አምላክ መንበረ ዳዊት አቡሁ ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም ፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ) ማርያም ሆይ ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ ፡ እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። ይህ ታላቅ ይኾናል ፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል ። እግዚአብሔር አምላክም የአባቱ ዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ።

በያዕቆብም ፡ ቤት ለዘለዓለም ይነግሣል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ብሎ ያበሰራትን ሞገሳዊ ጸጋ በመ ሥልከትና በማድነቅ ነው ። ሉቃ ምዕ ፩ ቁ ፴፩–፴፫ ።



በስድስተኛው ወር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የጌታን ልደት ለማብሰር ወደ እመቤታችን ተላከ ። ሉቃስ ምዕ ፩ ቁ ፳፮ ።

www.ethiopianorthodox.org

በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኁብርት ያለው በድንግልና ሥጋ በድንግልና ነፍስ ጸንታ መገኘቷን ያመለክታል ።

የዚህን ዓለም ነገሥታት የወለዱ ሴቶች ፣ ንግሥታት እየተባሉ ሲከበሩ ፤ በያዕቆብ ቤት ለዘለዓለም ይነግሣል ፤ የተባለውን የባሕርይ ንጉሥ ፤ የባሕርይ አምላክ ፣ የወለደች ቅድስት ድንግል ንግሥትነ እግዝእትነ እየተባለች ልትከበር እንዴት አይገባትም ? ።

የዚህ ዓለም ንግሥታት ወደ ነገሥ ልጃቸው እያማለዱ ሰውን ሲያስጠቅሙ፣ በመልአኩ ቃል ከእግዚአብሔር ባለሟልነትን ፣ አገኘሽ የተባለች እመቤታችን ወደ እግዚአብሔር አማልዳ ሰውን ልታስጠቅም አይቻላትም እንዲት ይባላል ? ።

፪ኛ/ ንጽሕት እያልን የምንወድሳት ፣ ነቢዩ ኢሳይያስ በንጽሐ ሥጋ በንጽሐ ነፍስ ፣ በንጽሐ ልቡና ፍጽምት ፣ ኸና አምላክን መውለዷ አስቀድሞ በመንፈስ እግዚአብሔር ተገልጦለት ፣ (በእንተ ዝንቱ ይሁበክሙ እግዚአብሔር ትእምርተ) ሰለዚህም ፣ እርሱ እግዚአብሔር ምልክትን ይሰጣችኋል ያለውን ሲያስረዳ (ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል) እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጸራዋለች ብሎ በትንቢት የተናገረውን ልዕ



ልናዋን በማረጋገጥ ነው ። ኢሳ ም ፯ ቍ ፲፬-፲፭ ። ማቴ ም ፩ ቍ ፳፫–፳፬ ።

፫ኛ/ ቡርክት እያልን የምንወድሳት ፤ ከልዑል እግዚአብሔር ለታላቅ ምሥራች የተላከ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፤ቡርክት አንቲ እምአንስት (በሴቶች ዘንድ የተባረክሽ ነሽ ያለውንና መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ኤልሳቤጥ (ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ። ምንትኑ አነ ከመ ትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ) አንቺ በሴቶች ዘንድ የተባረክሽ ነሽ ፣ የሆድሽም ፍሬ የተባረከ ነው ። የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጪ ዘንድ ለኔ እንዴት ይገባኛል ብላ የተናገረችውን ቃለ አክብሮ መሠረት በማድረግ ነው ። ሉቃ ም ፩ ቍ ፵፩–፵፭ ።

፬ኛ/ ብፅዕት እያልን የምንወድሳት ፤ መንፈስ ቅዱስ አናግሮ ሥራ ያሠራት ኤልሳቤጥ (ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር) ስለ አንቺ የተነገረው ቃል እንዲፈጸም ለምታምኚ ለአንቺም ምስጋና ይገባሻል ያለችውንና ራሷ እመቤታችን (ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ። እስመ ገብረ ሊተ ኃይለ ዐቢያተ ወቅዱስ ስሙ) እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል። እርሱ ብርቱ የሚሆን ታላቅ ሥራን በኔ ሠርቷልና ስሙ ቅዱስ ነው ብላ የተናገረችውን ይዘን ነው ። ሉቃ ም ፩ ቍ ፵፮—፵፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ኛ/ ምልእተ ጸጋ ምልእተ ክብር እያልን የምናከብራትና የምንወድሳት፤ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል (ተፈሥሒ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ) ጸጋን የተመላሽ ሆይ ፡ ደስ ይበልሽ ፡ እግዚአብሔር ከንቺ ጋራ ነው ብሎ ያበረከታትን አምኃ ሰላም ተከታትለን ነው ። ሉቃ ም ፩ ቁ ፳፰ ።

ይህ ሁሉ ዘለዓለማዊ ክብር የተሰጣት ስትኾን ፤ አታማልድም ፡ ለኃጥአን አትራራም ብሎ መካድ በእርሷ መመረጥ ላይ የተመሠረተውን የእግዚአብሐርን ቸርነት መካድ ይኾናል ።

የእግዚአብሔር ቸርነትም በርእሷ ላይ መመሥረቱን (መገለጡን) ከዚህ የሚከተሉት ጥቅሶች ያስረዱናል ።

፩ኛ/ ቀድሞ በዘመነ አበው (ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም) እግዚአብሔር በሴም ቤት (ድንኳን) ይደር ተብሎ በኖኅ ልሳን የተነገረው ተስፋ የተፈጸመው በእርሷ ነው ። ኦሪ ዘፍ ም ፱ ቁ ፳፯ ።

፪ኛ/ እንዲሁ በዘመነ አበው(በዘርዕከ ይትባረኩ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር) የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርኽ ይባረካሉ ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል ለአብርሃም የተነገረው ተስፋ የተፈጸመው በእርሷ ነው ። ኦሪ ዘፍ ም ፲፪ ቁ ፫ ግብረ ሐዋርያት ም ፫ ። ቁ ፳፭ ።



፫ኛ በዘመነ ነገሥት (መሐለ እግዚአብሔር ለዳዊት በጽድቅ ወኢይኔስሕ እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ) እግዚአብሔር ለዳዊት ከሆድኽ ፍሬ ብዙፋንኽ ላይ አስቀምጣለሁ ሲል በውነት ማለ ፤ ከርሱም አይርቅም ተብሎ ለዳዊት የተነገረው ተስፋ የተፈጸመው በእርሷ ነው ። መዝ ፻፴፩ ቁ ፲፩። ግብረ ሐዋ ም ፪ ቁ ፴ ።

ይህ ስለእርሷ የተነገረው ትንቢታዊ ቃል እንደሚያስረዳን ፤ ቅድመ ዓለም በአምላክ ሕሊና የተመረጠች እርሷ እመቤታችን ከአዳም እስከ ሴም ፤ ከሴም እስከ አብርሃም ፤ ከአብርሃም፤ እስከ ዳዊት ፤ ከዳዊትም እስከ አባቷና እናቷ (እስከ ኢያቄምና ሐና) ዘመን ድረስ ከባሕርይ ወደባሕርይ እየተከፈለች ፤ ከትንቢት ወደትንቢት፤ ከተስፋ ወደተስፋ እየተሸጋገረች ፤ ከአብራከ ኢያቄም ከማኅፀነ ሐና ተወልዳ በንጽሐ ሥጋ ፤ በንጽሐ ነፍስ ፤ በንጽሐ ልቡና (በድንግልና ሥጋ ፤ በድንግልና ነፍስ) ፍጽምት ሆና ብትገኝ፤ ዓለምን ሁሉ ከኃጢአት ፍዳ የሚያድን አምላክን ስለወለደች፤ ቀድሞ ገና በባሕርየ አዳም ውስጥ ሳለች ተስፋ ሥጋ ፤ ተስፋ ነፍስ እንደሆነች ፤ ዛሬም እመ አምላክ ፤ ወላዲተ ፤ አምላክ ፤ እንዲሁም ንግሥት ፤ ንጽሕት ፤ ቡርክት ፤ ብፅዕት ምልእተ ጸጋ ምልእተ ክብር ተብላ በምትመሰገንበት ጊዜ ፤ በልጅዋ በክርስቶስ ላመኑ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ተስፋ ሥጋ

www.ethiopianorthodox.org

ተስፋ ነፍስ ኾናለች እንጂ ፡ ከፈጣሪነቱ ፡ ከፍጡራን በላይ ሆና የተሰጣት መንፈሳዊ ክብር የተለወጠበት ምክንያት የለም ።

ምስጋና የተገባት መሆኗንም ከዚህ በላይ የጠቀስነው የወንጌሉ ቃል እንደአስረዳን ፡ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል በብፅዕት ኤልሣቤጥ እንደበት ከከበረችና ከተመሰገነች ፡ ድኅነተ ነፍስን ያገኘንበት ስንሆን ፡ በኛ እንደበት ንግሥት ፤ ንጽሕት ፡ ቡርክት ፡ ብፅዕት ፡ ምልእተ ጸጋ ፡ ምልእተ ክብር ተብላ መመስገን እንዴት አይገባትም ? ብለን አማላጅነቷንና ከፍጡራን በላይ መክበሩዋን የሚጠራጠረውን ሕሊና እንቃወማለን ።

## ለወላዲተ አምላክ ሰጊድ ስለሚገባ ።

ወላዲተ አምላክ ፤ እመ አምላክ እንደመሆኗ መጠንም ፡ ሰጊድን እንድናቀርብላት ብዙ ቀዱሳንና የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በየድርሰታቸው ማስረጃ ሰጥተውናል ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፡ ትልቁ የቢስክስ ኤጲስቆጶስ የነበረው ሊቁ ኤራቅሊስ ፤ አረጋዊ ዮሴፍ ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ በግብረ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ቃልን መፅነሷን ከመልአኩ ቃል ሰምቶ እንደሰገደላት ሲያስረዳ (ወሰበ ሰምዐ ዮሴፍ ዘይቤሎ መልአከ እግዚአብሔር አ ዮሴፍ ኢትፍራህ ነሢአታ ለማርያም ። እስመ ዘእም ላዕሌሃ ይትወለድ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ ፤ ሰገደ ለድንግል ወገነየ ለንጽሓ ፤ ወአእመረ ከመ ይእቲ ድንግል ዘተናገረ በእንቲአሃ ኢሳይያስ ነቢይ በትንቢት እንዘ ይብል ናሁ ድንግል ትፀንስ ፤ ወትወልድ ወልደ ፤ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል) ዮሴፍ የእግዚአብሔር መልአክ ዮሴፍ ሆይ ፡ ከእሷ የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ ነውና ፤ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ ብሎ ሲነግረው በሰማ ጊዜ ለድንግል ሰገደ ፡ ንጽሕናዋንም አመነ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢት ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ፤ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል ብሎ የተናገረላት ድንግል እንደ ኾነችም ዐወቀ ብሎ በሃይማኖተ አበው ተናግሮዋል ። ሃይ አበ ኤራ ክፍል ፫ ።

የኢትዮጵያ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ፤ ይህንን የሊቁን የኤራቅሊስን ቃል አረጋግጦ ( አእሚሮ ዮሴፍ ንጽሐ ሥጋሃ ለማርያም ሰገደ ላቲ ወአምኃ ) ዮሴፍ ለማርያም ድንግልናዋን ዐውቆ ሰገደላት ፤ እጅ ነሣትም ብሏል የእመቤታችንን ድጓ ተመልከት ።

ስለዚህ ፤ በንጽሕናዋ በቅድስናዋ ተመርጣ አምላክን መውለዷን ( ጌታን ከመውለዷ አስቀድሞ ድንግል ንጽሕት ፡ ጌታንም ከመውለዷ በኋላ ድንግል ንጽሕት መሆኗን ) እንዲሁም በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ፤ በቅድስት



www.ethiopianorthodox.org

ኤልሳቤጥ ቃል ምልእተ ጸጋ ቡርክት ብዕሲት ተብላ መመስገኗን እየተመለከትን ፡ ለዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ በዕለተ ስቅለት ያደራ እናትነቷ ሲሰጠው ፡ ለእኛም እንደተሰጠን ዐውቀን ከፍጡራን በላይ በመከበሯ የአክብሮት ሰጊድን እያቀረብን ልንማጠናትና በመንፈሳዊ ተጸምዶ ልናገለግላት ተገብቶናል ።

የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ፤ ሥርዓተ አበውን ተከትለው ለማርያምሰ ዘንሰግድ ላቲ እስመ ነሥአ ሥጋ እምኔሃ እግዚአብሔር ፈጣሪሃ ፤ ወረከብነ ንሕነ መድኃኒተ እምኔሃ ብለው የአክብሮት ሰጊድ እንድናቀርብላት አዘዋልና መንፈሳዊ ተፀምዶ የሚገባት መሆኑ በብዙ ሊቃውንት ቃል የተመሰከረ ነው እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደወኃ ፈሳሽ አይደለም ።

## ፬ኛ ምዕራፍ ።

## ስለ ጻድቃንና ስለ ሰማዕታት አማላጅነት ።

አንዳንድ ሰዎች ጻድቃን ያማልዳሉ ፤ ሰማዕታት ይራራሉ ፤ ቅዱሳን ስለ ኃጥአን ይለምናሉ ። ማለት በፍጹም ሐሰትነው እያሉ በየመጻሕፍቱ የተነገረውን ቃል ማስተባበላቸው ይሰማል ።

ይልቁንም ከአቤል ጀምሮ የሞቱ ጻድቃን ስለኃጥአን መለመናቸው ቀርቶ በሚያስቸኩል ቃል ሰውን ለማጥፋት በጭከና እያማረሩ ፤ እየከሰሱም ሁልጊዜ በመጮ ያሳጣሉ እንጂ ስለ በጎ ነገር ፈጣሪያቸውን አይለምኑም በማለት በራእየ ዮሐንስ ም ፮ ቍ ፱—፲፩ የተጻፈውን እየጠቀሰ ነቅሮዋቸዋል ።

በዚህ በኩል ያለውን ነቀፋና ስድብ ስንመለከተው ግን ፡ ጻድቃን ፤ ሰማዕታት ከሞቱ ፡ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ለማመልከት ችሎታ እንዳላቸው አምኖልናል ።

በዐፀደ ነፍስ ሆነው ደማቸውን በፈሰሱ ዐላውያን ላይ አቤቱ ስለ ፈሰሰው ደማችን ጠላቶቻችንን አትበቀልልንምን ? (በቶሎ አትፈርድባቸውምን ? ብለው ወደፈጣሪያቸው ማመልከት የቻሉ ጻድቃን ፤ ሰማዕታት ፤ ትምህርታቸውን ፤ ተአምራታቸውን በክርስቶስ ስም አክብረው ለተቀበሉ ፤ ነቢይነታቸውን ፤ ሐዋርያነታቸውን ፤ መምህርነታቸውን ፤ ጻድቃንነታቸውን በክርስቶስ ቃል ተቀብለው ለተማጠኑዋቸው ክርስቲያኖች ማመልከትና ማማለድ ይቻላቸዋል ቢባል ከቅዱስ መጽሐፍ የተለየ አሳብ የለበትም ።

አማላጅነት አንዳንድ ጊዜ እንደየሥራው መጠን አንዱን ጠቅሞ አንዱን ለመጕዳት ሆኖ ይገኛል ።

እንዲህ ከሆነ ፤ አማላጅ ፤ ክፉ ፡ ሥራ የሠራውን ዐመፀኛ ለማስቀጣት ያደረገውን ምልጃ ፡ ብቻ ተመልክቶ በበጎ በኩል ያለውን የአማላጅነቱን ችሎታ ከቃሪክ ውስጥ ለመፋቅ ይችላልን ?



www.ethiopianorthodox.org

ተቃዋሚው ሰው ጻድቃን ሰማዕታት በዐጸደ ነፍስ ሆነው ተአምራት ማድረግና ማማለድ (የሕያውነት ሥራ መሥራት) የማይቻላቸው ስለመሰለው ፤ ጻድቃን ፤ ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ እርዱን አማልዱን ፤ እያላችሁ ብትጮሁ አይሰሟችሁም ። አንድ ጊዜ በሞት አንቀላፍተው ሬሳዎች ሆነዋልና (የሞት እንቅልፍ ይዟቸዋልና) የሕያውነት ሥራ ለመሥራት አይችሉም ብሏል ።

እንዲህ ማለቱ ግን ፡ ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሰውን የወንጌሉን ቃል በዓይነ ልቡና ፡ ባያስተውለው ይመስላል ።

ቃለ ወንጌሉ (ኢያንበብክሙሁ ዘተብህለ ለክሙ እም ኀበ እግዚአብሔር ዘይቤ አነ እግዚአብሔር አምላከ አብርሃም ፤ ወአምላከ ይስሐቅ ፡ ወአምላከ ያዕቆብ ፡ አምላከ ሕያዋንኬ ውእቱ ወአኮ አምላከ ምዉታን) ከእግዚአብሔር ዘንድ የተባለውን አላነበባችሁምን ? እኔ እግዚአብሔር የአብርሃም አምላክ ፤ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ ። እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ጻድቃን ሰማዕታት የእግዚአብሔር ወዳጆች የኾኑ ቅዱሳን ሁሉ በሕይወተ ነፍስ ሕያዋን ሆነው መኖራቸውን ነግሮናል ። ዘፀ ም ፫ ቍ ፮ ። ማቴ ፡ ም ፳፪ ቍ ፴፩-፴፫ ። ማር ም ፲፪ ቍ ፳፮ ። ይልቁንም ቅዱስ ሉቃስ የጻፈው ወንጌል እላይ የተጠቀሰውን



ቃል እንዲሁ ከተናገረ በኋላ (ኢኮነኬ አምላከ ምዉታን አላ አምላከ ሕያዋን ውእቱ ። እስመ ኵሎሙ ሕያዋን እሙንቱ በኀቤሁ) እግዚአብሔር የሙታን አምላክ አይደለምና፡ የሕያዋን እንጂ ፡ ሁሉ በርሱ ዘንድ ሕያዋን ናቸውና ብሎ ጻድቃን፡ ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ በዐፀደ ነፍስ የሕያውነት ሥራ መሥራታቸውን አጕልቶ ተናግሮዋል ። ሉቃ ም ፳ ቍ ፴፰ ።

እንዲህ ተብሎ የሞት ሥልጣን ሳይወስናቸው በሕያውነት መኖራቸው በወንጌል ቃል ከተመሰከረ የሞት እንቅልፍ ይዟቸዋልና ስትለምኗቸው አይሰሟችሁም እንዴት ይባላል ? ለነቃፊው፡ ዕዝነ ሥጋቸው በሞት ሲደነቍር ዕዝነ ነፍሳቸው በሞት የደነቈረ መሰለውት ይኾን ? ወይስ፤ እነሙሴ፡ እነአሮን፡ ከእነርሱም በኋላ የተነሡ ነቢያት፤ ሐዋርያት ፤ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት ፡ አምላከ አብርሃም ፤ አምላከ ይስሐቅ ፤ አምላከ ያዕቆብ እያሉ ሲለምኑት ያላፈረ አምላክ ፤ አምላከ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፤ አምላከ አቡነ ዜና ማርቆስ ፤ አምላከ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፤ አምላከ ቅዱስ ቂርቆስ ማረን ይቅር በለን እያልን ስንለምነው የሚያፍር መስሎት ይኾን ።

ቅዱስ ጳውሎስ ፡ ልዑል እግዚአብሔር በነፍስ ሕያዋን ሆነው መንግሥተ ሰማያትን ያወርሰናል በማለት በዓይነ ተስፋ የሚመለከቱት የወዳጆቹ አምላክ በመባሉ

www.ethiopianorthodox.org

የማያፍር መሆኑን ሲያስረዳ ፤ ወይእዜሰ ተፀውቀ ከመ
እንተ ትኄይስ ሀገረ እንተ በሰማያት ኮኑ ይሴፈዉ ። ወበ
እንተዝ ኢየኀፍር እግዚአብሔር ከመ ይትበሀል አምላ
ከሙ ። እስመ አስተዳለወ ሎሙ ሀገረ) እንግዴህስ በሰ
ማይ ያለች ፤ የምትበልጠውን አገር ተስፋ ያደርጉ እን
ደነበረ ታወቀ ፤ ስለዚህም ፤ እግዚአብሔር አምላካቸው
ይባል ዘንድ አያፍርም ። ተስፋ ያደረጓትን አገር አዘጋጅ
ቶላቸዋልና ብሎ ነግሮናል ። ዕብ ም ፲፪ ቊ ፲፯ ።

የእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን ሁሉ ፤ በዐጸደ ነፍስ
ሕያዋን ሆነው የመንግሥተ ሰማያትን ተስፋ መጠባበ
ቃቸውን ሐዋርያው እየነገረን ፤ የሞት እንቅልፍ የያዛ
ቸው ሬሳዎች (በድኖች) ሆነዋልና የእናንተን ልመና
መስማት አይቻላቸውም ማለት (በወንጌል ቃል ሕያዋን
የተባሉትን ጻድቃን ፤ ሰማዕታት ሬሳዎች ብሎ መሳደብ)
ከወንጌል ቃል መተላለፍ አይሆንምን ?

እኛ ግን ፤ እላይ እንደተናገርነው በዘመነ ብሉይ
የነበሩ አባቶች ፤ መቅሠፍት ወይም መከራ በደረሰባቸው
ጊዜ (ተዘከር አብርሃምሃ ፤ ተዘከር ይስሐቅሃ ተዘከር ያዕ
ቆብሃ) አብርሃምን አስብ ይስሐቅን አስብ ያዕቆብን አስብ
እያሉ የቀድሞውን ኪዳናዊ ቃል ሲያዘክሩ ፤መዓቱ በም
ሕረቱ ይመለስላቸው እንደነበረ አልዘነጋንም ኦሪ ዘጸአ
ም ፴፱ ቊ ፳፯ ። ኦሪ ዘሌ ም ፳፮ ቊ ፵፪ ።



ሆኖም ፡ ቀድሞ በዘመነ ብሉይ ለወዳጆቹ ለአብር
ሃም ፤ ለይስሐቅ ፤ ለያዕቆብ የሰጠኋቸውን ኪዳኔን አስ
በለሁ እያለ የምሕረት ፤ የቸርነት ሥራውን ሲሠራ እን
ደኖረ ፡ አሁንም በዘመነ ሐዲስ ነቢዩን በነቢዩ ስም የተ
ቀበለ የነቢዩን ዋጋ ይወስዳል ። ጻድቁን በጻድቁ ስም የተ
ቀበለ የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ብሎ የተናገረውን ቃሉን
መሠረት በማድረግ ለተቸገሩ ድኖች ወንድሞቻቸው
በጻድቃን በሰማዕታት በእመቤታችን በቅድስት ድንግል
ስም የርኅራኄን ተግባር ለፈጸሙ ክርስቲያኖች የምሕ
ረት የቸርነት ሥራውን ይሠራላቸዋል ። (ዋጋቸውን
ይከፍላቸዋል)

ስለዚ፤ህ በዘመነ ብሉይ የነበሩ አባቶች ለአብርሃም ፤
ለይስሐቅ ፤ ለያዕቆብ የሰጣቸውን ኪዳኑን ባሳሰቡ ጊዜ፤
መለኮታዊ ቃሉ መዓቱን መቅሠፍቱን እንደአራቀላቸው ፤
እኛም ለቅድስት ድንግል ማርያም ፤ ለጻድቃን ፤ ለሰማ
ዕታት የሰጣቸውን ኪዳኑን ባሳሰብን ጊዜ ፡ መለኮታዊ
ቃሉ መዓቱን መቅሠፍቱን በምሕረቱ እንዲመልስልን
እናምናለን ።

የሆን ሆኖ ፤ ጻድቃን ፤ ሰማዕታት በዚህ ዓለም ከተ
ቀበሉት ልዩ ልዩ ፈተና ተለይተው በአካለ ነፍስ ወደዘ
ለዓለማዊ ቦታቸው ከሔዱ በኋላ ፤ በጣዕም ላይ ጣዕም፡በጸጋ
ላይ ጸጋ፡ በብርሃን ላይ ብርሃን ፡ እየተጨመረላቸው በሕያ

www.ethiopianorthodox.org

ውነት ፤ በባለሟልነት ይኖራሉ እንጂ የሞተ ሥጋ ሥልጣን ክብራቸውን (ባለሟልነታቸውን) ሊቀንስባቸው አይችልም ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፤ ወንጌል እንዲህ ብሎ ይነግረናል ።

(ወናሁ አስተርአይዎሙ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ ምስሌሁ ለእግዚእ ኢየሱስ) ማቴ ም ፲፯ ቁ ፫ ። እነሆ ሙሴና ኤልያስ ከጌታ ኢየሱስ ጋራ ሲነጋገሩ ለእርሳቸው ታዩዋቸው ።

በዚህ ጊዜ ፤ ኤልያስን ከሕያዋን ፤ ሙሴን ከሙታን መካከል ስለጠራቸው ፤ የኤልያስ መታየት በአካለ ሥጋ ሲኾን ፤ የሙሴ መታየት በአካለ ነፍስ እንደ ኾነ የታወቀ ነው።

ሙሴ ከሞተ ጀምሮ ፤ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ያለው ጉልቄ ዘመን አንድ ሽህ ስድስት መቶ አርባ ስድስት ዘመን መሆኑ ይነገራል ።

እንዲህ ከሆነ ፤ ሙሴ ከዐጸደ ሥጋ ወደ ዐጸደ ነፍስ ተዘውሮ ብዙ ዘመን ከሆነው በኋላ፤ በደብረ ታቦር ከሕያዋን ጋራ ተገኝቶ ፡ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ በባለሟልነት ሲነጋገር የታየ ሲኾን፤ ጻድቃን ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ ሬሳዎች በድኖች ናቸውና ወደ ፈጣሪያቸው ለማመልከት ፤ ከፈጣሪያቸው ጋር ቃል ለቃል ለመነጋገር አይችሉም ማለት ይገባልን ?



በዚያውስ ላይ ገና በሀብተ ልደት ያልታደሰ ሙሴ በአካለ ነፍስ ከፈጣሪው ጋር የባለሟልነት ንግግር ከደረገ፤ በሀብተ ልደት ፍጹማን የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ጻድቃን ሰማዕታት በዐፀደ ነፍስ የባለሟልነት ንግግር ከማድረግ እንዴት ይገታሉን ።

ግርማ መለኮት በታየበት በደብረ ታቦር የተገለጠውን ይህንን የሙሴን ባለሟልነትና የነፍስ ሕያውነት እያሰብን፤ጻድቃን ፤ ሰማዕታት ከዚህ ዓለም ፃዕር ጋር ፤ጻማ ፤ ሕማም በረፉ ጊዜ ፤ በጣዕም ላይ ጣዕም ፤ በጸጋ ላይ ጸጋ ፤ በብርሃን ላይ ብርሃን ፤ በዕውቀት ላይ ዕውቀት ይጨመርላቸዋል እንጂ የሞት ሥልጣን በዐፀደ ነፍስ የሚሰጣቸውን ጸጋና ዕውቀት ሊገታባቸው አይችልም እንላለን ።

ቅዱስ ጳውሎስም ፤ በዐጸደ ነፍስ የሕያውነትን ሥራ መሥራታቸውንና የክርስቲያን አለኝታ ለመሆን መቻላቸውን ሲያስረዳ፤ በመጋዝ ተሰንጥቀው በደንጊያ ተወግረው፤ በሰይፍ ተመትተው ሞቱ ካለ በኋላ፤ እንደ ደመና የሚከቡን እነዚህ ሁሉ ምስክሮች ያሉን እኛም የከበደውን ሸክም ሁሉ ፤ የኃጢአትንም ተብትብ ከላያችን እንጣል ብሎ ክብራቸውን ተናግሮዋል። ዕብ ም ፲፪ ቁ ፩ ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ሰማዕታት ከሞቱ በኋላ ፤ ዕውቀትና ክብር እንደሚጨመርላቸው ሲያስረዳ ፤(በከመ

www.ethiopianorthodox.org

ወልደ ንጉሥ እንዘ ሀሎ ውስተ ማኅፀነ እሙ ኢየአምር ምንተኒ ፤ ወእም ድኅረ ተወልደ ይነብር ዲበ መንበረ መንግሥት ፤ ወይመልክ ኵሎ ፤ ከማሁኬ ሥርዓት ዘበህየ) የሚነግሥ የንጉሥ ልጅ በናቱ ማኅፀን ሳለ ምንምን እን ዳያውቅ ፤ ከተወለደ በኋላ እንዲነግሥና ሁሉን እንዲገዛ በዚያኛው ዓለም ያለው ሥርዓት እንደዚሁነው ብሎ ተና ግሮዋል ። ዮሐ አፈ ወ ተግ ፮ ።

መተርጒማንም ይህንኑ የሊቁን አነጋገርና የመጻሕ ፍትን ቃል ተከትለው ጻድቃን ከበቁ በኋላ የሚያውቁት ዕውቀት ፤ ሕፃናት ተወልደው እስከ ሰባት እስከ ዐሥራ ሁለት ዓመት እንደሚያውቁት ዕውቀት ነው ። ጻድቃን ከሞቱ በኋላ ፤ በገነት (በዐጸደ ነፍስ) የሚያውቁት ዕውቀት ሕፃናት እስከ ኻያ ፤ እስከ ሠላሳ ዓመት እንደሚያውቁት ዕውቀት ነው ። ጻድቃን መንግሥተ ሰማያት ገብተው የሚያውቁት ዕውቀት ፤ ሕፃናት እስከ አርባ ፣ እስከ አምሳ ዓመት እንደሚያውቁት ዕውቀት ነው እያሉ ምሳሌ በመ ስጠት ክብራቸውን በየደረጃው ለይተው አስረድተዋል ።

ቅዱስ ጳውሎስም ከሞተ በኋላ የሕያውነትን ክብር ማግኘቱን ሲያስረዳ ፤ (እፈቱስ እፍልስ ፤ ወአሀሉ ኀበ ክር ስቶስ ። ወፈድፋደ ይኄይስ ወይደሉ ሊተ ዝንቱ) ነገር ግን በክርስቶስ ዘንድ ለመኖር ከዚህ ዓለም ተለይቼ ልሔድ እወዳለሁ ። ይልቁንም ይህ ለኔ የሚበልጥና የሚገባ ነው ብሏል ። ፊልጵ ም ፩ ቍ ፳፫ ።



የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወ ርቅም ፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ አራት መቶ ዘመን ከመላው በኋላ ለቅዱስ ጳው ሎስ በአካለ ነፍስ የተሰጠው ክብር በጸጋ እግዚአብሔር ተገልጦለት እንዲህ ብሏል ።

(ወባሕቱ ብፁዕሰ ጳውሎስ ኢኮነ በዝንቱ አርአያ ፤ ወትእምርተ ዝንቱ ። እስመ ውእቱ ነበረ ኵሎ መዋዕለ ሕይወቱ ፣ እንዘ ያበርህ ወያንፀበርቅ ። አኮ አሐደ ዕለተ ወኢ ክልኤተ ወኢ ዐሠርተ ወኢ ዕሥራ ወኢ ሠላሳ ፣ አላ ናሁ ኀለፈ አርባዕቱ ምእት ዓመት እም ዘአዕረፈ ። ወሀለወ እስከ ይእዜ እንዘ ይትዌስክ ሥን በዲበ ሥን ወፈድፈደ ክብሩ እምዘቀዳሚ አመ ሀሎ ሕያወ ውስተ ምድር) ተግ ሣጽ ፱ ገጽ ፻፺፯ ።

ብፁዕ ጳውሎስ ፤ በዚህ ዓለም ከብረው ኑረው ከሞቱ በኋላ ፣ በወዲያኛው ዓለም ክብር እንደሌላቸው ሰዎች አይደለም ። ይህንንም የሚያስረዳ ነገር ፣ በዚህ ዓለም በነበረበት ዘመን ሁሉ በትምህርቱ በተአምራቱ ለምእ መናን ሁሉ ሲያበራ ኑሯል ።

ያበራላቸውም አንዳንድ ቀን አይደለም ። ሁለት ሁለት ቀን አይደለም ። ዐሥር ዐሥር ቀን አይደለም ። ኻያ ኻያ ቀን አይደለም ። ሠላሳ ሠላሳ ቀንም አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

እነሆ ከአረፈ አሁን አራት መቶ ዘመን ኾኖታል ። ሆኖም፡ እስከ ዛሬ ድረስ በብርሃን ላይ ብርሃን ፡ በክብር ላይ ክብር ሲጨመርለት ይኖራል ።

በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ ሳለ አግኝቶት ከነበረው ክብር ፡ ከሞተ በኋላ ያገኘው ክብር በልጧል ። ከዚህም አያይዞ (ወሥናሙሰ ለቅዱሳን ዘበሰማያት መኑ ይክል ፈጽሞ ነጊሮቱ) በሰማይ የሚገኘውን የቅዱሳንን ክብር ጠንቅቆ መናገር የሚችል የለም ብሏል ።

ቅዱስ ጳውሎስ ፡ ከዚህ ዓለም ድኩም ዐርፎ አራት መቶ ዘመን ከሆነው በኋላ ፡ ሊቁ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በክብር ላይ ክብር ሲጨመርለት ይኖራል ብሎ መመስከሩ ፡ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ካረፉ በኋላ ገድላቸው እየተነበበ ፡ ስማቸው ፡ እየተጠራ ፡ ዝክራቸው እየተዘከረ ፡ በክብር ላይ ክብር እየተጨመረላቸው በሕይወተ ነፍስ መኖራቸውን የሚያስረዳ ነው ።

መንፈሳዊ ተጋድሎዋቸውን ፈጽመው ፡ ፈጣሪያቸውን በሚገባ አገልግለው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ወደ በለጠ በታ ፡ ወደ በለጠ ክብር የሔዱ ቅዱሳን ጻድቃን ፡ ሰማዕታት በሕይወተ ነፍስ ሕያዋን ሆነው ከመኖራቸው በላይ ፡ በብርሃን ላይ ብርሃን በጸጋ ላይ ጸጋ ፡ በዕውቀት ላይ ዕውቀት ፡ በጣዕም ላይ ጣዕም ፡ ገና እየተጨመረላቸው ሳሉ ፡ አንዳንድ ተጠራጣሪ ሞተ ሥጋ ጸጋቸውን



እንደሚቀንስባቸው አስመስሎ የማይሰሙትን ምውታን (የሬሳችን) ስም ብታነሡ ትጸድቃላችሁ ብላችኋል እያለ እኛንም አበቶቻችንንም ፡ ልዑል እግዚአብሔር ያከበራቸውን ጻድቃንና ሰማዕታትንም ነቅፎዋል ።

እኛ ግን፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዐስበ ጻድቅ ይነሥእ ብሎ ያከበራቸውን ጻድቃንን ፡ ሰማዕታትን ፡ ማክበራችን ዕዳ በደል እንዳይኾንብን፤ አምልኮተ እግዚአብሔርንም እንዳይለውጥብን ዐውቀን ቅዱስ ወንጌሉን እንከተላለን እንጂ የማናቸውም ተጠራጣሪ መንፈስ አያናውጸንም ።

---

## ፳፫ኛ ምዕራፍ ስለ አክብሮት ስግደት ።

በጸጋ እግዚአብሔር ለከበሩ ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ፡ ጻድቃን ፡ ሰማዕታት የአምልኮት ሳይሆን የአክብሮት ስግደት ማቅረብ እንዲገባ ብዙ መጻሕፍት ማስረጃ ይሰጡናል ።

ይሁን እንጂ ፡ ከቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የራቁ አንዳንድ ሰዎች ስግደት ፈጣሪና ፍጡር፡ የሚያመልክና ተመላኪ ተለይተው የሚታወቁበት ስለ ኾነ ፡ ከእግዚአብሔር በቀር ለሌሎች አይሰጥም ብለዋል ።

አምላካችንም ኢታምልክ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ ፡ ወኢትግበር ለከ ሥዕለ ፡ ወኢምሳለ ። ኢትስግድ ሎሙ ወኢታምልኮሙ ። እስመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ

www.ethiopianorthodox.org

ቀናኢ ፣ ወእሳት በላዒ ብሎ የሰጠንን ትእዛዝ እየጠቀሱ እግዚአብሔር ጸጋውን አድሎ ላከበራቸው ወዳጆቹ የአክብሮት ስግደት ማቅረባችንን ሲነቅፉና አምልኮተ እግዚአብሔርን የለወጥን ሲያስመስሉ ይሰማሉ ።

ነገራቸውንም እየዘረዘሩ በታቦት፣በመልአክ ፣ በጻድቅ፣ በሰማዕት ፣ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ጸጋ በተሰጣቸው ቃላላቅ ሰዎችም ፊት መስገድ አምልኮተ እግዚአብሔርን ከመለወጥ የሚያስቈጥር ነው ብለዋል ።

ስለዚህ ፣ የአክብሮት ስግደት ከጥንት ከመሠረት ተያይዞ የመጣ መሆኑን ቀጥለን እናስረዳለን ።

፩ኛ በታቦተ እግዚአብሔር ፊት መስገድ ስለተገባ ።

ቀድሞ ፤ ልዑል እግዚአብሔር ለወዳጁ ፣ ለባለሟሉ ሙሴ ታቦትን የሰጠው እኔን ትተኸ ጣዖት አምልክ ፣ ለጣዖት ስገድ ብሎ ሳይሆን ፣ በታቦት አድሬ አምልኮቴን እገልጥልኻለሁ ሲለው በመሆኑ ፣ ሙሴ ኢያሱ ዳዊት እስራኤል ሁሉ በታቦት ፊት ሰግደዋል ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፣ አሪት ዘኢያሱ (ወሰጠጠ አልባሲሁ ኢያሱ ፣ ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር ወሰገደ ቅድመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር እስከ ሠርክ ውእቱ ፣ ወኵሎሙ እስራኤል) ኢያሱም ልብሱን ቀደደ ፣ በእግዚአብሔር ታቦት ፊትም በምድር ላይ በግንባሩ ተደፋ ፣ (ሰገደ)



እስከ ማታ ድረስም እርሱና የእስራኤል ሽማግሎች ሁሉ በራሳቸው ላይ ትቢያ ነሰነሱ ይላል ። ኢያ ወል ም ፯ ቍ ፮ ።

ቢሆንም ፤ በታቦት ፊት መስገዳችን ቃለ እግዚአብሔር ስመ እግዚአብሔር ተጽፎበታል ፤ ማኅደረ እግዚአብሔር ነው ብለን ነው እንጂ ፣ የባሕርይ አምላክ ነው ብለን ፣ ወይም ከአንድ እግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን ዘንግተን አይደለም ።

፪ኛ ለመልአክ የአክብሮት ስግደት ማቅረብ ስለተገባ ።

እግዚአብሔርን በማገልገል ፤ ሰውን በመራዳት የሚኖሩ ቅዱሳን መላእክትን ፣ አክብረን የአክብሮት ስግደት እንድናቀርብላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ አርአያ ሰጥተውናል ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፣ በአሪት እንዲህ የሚል ንባብ እናገኛለን ።

(ወይቤሎ አንሰ መልአከ ኃይሉ ለእግዚአብሔር ወይእዜ በጻሕኩ ፣ ወወድቀ ኢያሱ በገጹ ውስተ ምድር ወሰገደ ሎቱ) እርሱም መለሰለት አለውም አይደለም፤ እኔ የእግዚአብሔር የሠራዊቱ አለቃ ነኝ ። አሁንም እኔ መጥቻለሁ ፤ ኢያሱም ወደምድር በፊቱ ወደቀ ፣ ሰገደለትም ኢያሱ ወልደ ነዌ ም ፭ ቍ ፲፬ ።

ዚና መዋዕል ቀዳማዊም የሚከተለውን ቃል ይነግረናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ወአልዐለ ዳዊት አዕይንቲሁ ፤ ወርእየ ለውእቱ መልአከ እግዚአብሔር እንዘ ይቀውም ማዕከለ ሰማይ ወምድር ወሰይፉኒ ምሉሕ ውስተ እዴሁ ፤ ወስፍሕት ውስተ ኢየሩሳሌም ፤ ወወድቀ ዳዊት በገጹ ወሰገደ ሎቱ፤ ወሊቃናት ሕዝብ ምስሌሁ ለቢሰሙ ሠቀ ወድቁ በገጸሙ) ዳዊትም ዓይኑን አነሣ፤ የእግዚአብሔርንም መልክተኛ በሰማይና በምድር መካከል ቁሞ ፤ በእጁም ሰይፍ ተመዞ ወደኢየሩሌምም ተዘርግቶ አየ ። ዳዊትና ሽማግሌዎችም ማቅ ለብሰው በግንባራቸው ወደቁ ። ፩ ዜና መዋዕል ም ፳፩ ቁ ፲፮ ። ምሥጢራትን ሁሉ የሚያውቅ ፍቁረ እግዚእ የሆነ ዮሐንስ ወንጌላዊም ለመልአኩ በመስገዱ እንደተሳሳተ አድርገው የሚገምቱ ሰዎች ፤ ዑቅ ኢትስግድ ሊተ እስመ አነሂ ገብር ዘከማከ ያለውን ንባብ ይዘው እንከራከርበት ይላሉ ። የአክብሮት ስግደት የማይገባ ቢሆን ሥልጣነ ሰማይ ወምድር የተሰጠው ሐዋርያ ለመልአኩ ሁለተኛ ጊዜ አይሰግድለትም ነበር ብለን እንመልስላቸዋለን ። ሐዋርያው ለመልአኩ በመስገዱ የተሳሳተ አድርገው መገመታቸው ፤ ማለት መልአኩ በሐዋርያው ላይ ያለውን ታላቅ ጸጋ ተመልክቶ ኢትስግድ ሊተ ማለቱን ምክንያት አድርገው መጥቀሳቸው በጥንተ ስብከት (ንዑ ትልወኒ) ኑ ተከተሉኝ ባለው መሠረት ጌታን ከተከተለ ጀምሮ ያልተሳሳተውን ሐዋርያ በጥንቃቄ ሊበል



ጡት አስበው ነውን ? ራእ ዮሐ ም ፲፱ ቁ ፲ ። ም ፳፪ ቁ ፰ ።

### ፫ኛ ለጻድቅ፣ ለሰማዕት የአክብሮት ስግደት ማቅረብ ስለተገባ ።

ቅዱሳት መጻሕፍት ለጻድቃን ፡ ለሰማዕታት ፤ እግዚአብሔር ጸጋውን ሰጥቶ ለአከበራቸው ደጋግ ሰዎች የአክብሮት ስግደት ማቅረብ እንዲገባ ፡ ብዙ ማስረጃ ይሰጡናል ።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ፡ አሪት ዘፍጥረት እንዲህ የሚለውን ቃል ይሰጠናል ።

(ወዮሴፍሰ መልእኩ ውእቱ ለብሔረ ግብጽ ፡ ወውእቱሰ ይሠይጥ ለኵሉ አሕዛበ ምድር ወሶበ መጽኡ አኃዊሁ ለዮሴፍ ሰገዱ ሎቱ በገጸሙ ውስተ ምድር) ዮሴፍም በምድር ላይ ገዢ ነበረ ። የዮሴፍም ወንድሞቹ በመጡ ጊዜ በምድር ላይ በግንባራቸው ሰገዱለት ። ኦሪ ዘፍ ም ፵፪ ቁ ፯ ።

ቀጥሎም እንዲህ ይላል ። (ይትቀነዩ ለከ አሕዛብ ወይሰግዱ ለከ መላእክት) አሕዛብ ያገለግሉኻል፤ አለቆችም ይሰግዱልኻል ። ኦሪ ዘፍ ምዕ ፳፯ ቁ ፳፱ ።

ዜና መዋዕል ቀዳማዊም ከዚህ የሚከተለውን ታሪክ ያስታውሰናል ። (ወወዕአ አርና እምጐርንሰ ወተ

www.ethiopianorthodox.org

ቀበሎ ለዳዊት ፡ ወሰገደ ሎቱ በገጹ ውስተ ምድር) ዳዊትም ወደ አርና መጣ አርናም ዳዊትን አየው ከዐውድማውም ወጣ ፡ በምድር ላይም ለዳዊት ሰገደለት ። ፩ ዜና መዋ ም ፳፩ ቍ ፳፩ ።

ግብረ ሐዋርያትም ፡ ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ከግዞት ቤት በተአምራት እምልጠው ቢሔዱ ፡ የግዞት ቤት ጠባቂ አክብሮ እንደሰገደላቸው ሲያስረዳ እንዲህ ይላል ። (ወእምጽአ ማኅቶተ ፡ ወሖረ እንዘ ይርዕድ እንተ ውስጥ ወሰገደ ኀበ ጳውሎስ ወሲላስ ወአውፅኦሙ አፍአ ወይቤሎሙ ምንተ እግበር እጋዕዝትየ ከመ እድኀን ።)

መብራትም አስመጥቶ ወደ ውስጥ ገባ ። እየተንቀጠቀጠም ለጳውሎስና ለሲላስ ሰገደ ። ወደውጪም አውጥቶ ጌቶቼ ሆይ ፡ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል አላቸው ። ግብ ፡ ሐዋ ም ፲፮ ቍ ፳፱ ።

ራእየ ዮሐንስም እንዲህ ይላል ። (ወይሰግዱ ቅድመ እገሪከ ፡ ወያእምሩ ከመ አነ አፍቀርኩከ ) እኔ እንደ ወደድኩኽ ያውቃሉ ከእግርኽ በታች ይሰግዳሉ ። ራእ ዮሐ ም ፫ ቍ ፱ ።

እንዲህ ሆኖ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረ ብዙ የአክብሮት ስግደት እያለ ፡ የአምልኮት እንጂ የአክብሮት ስግደት የለም ማለት ፡ ወይም ለጻድቅ ለሰማዕት ፡ ለሐዋርያ ፡ ለመልአክ ከሰገዳችሁ ፡ (ኢትስግድ ሎሙ



ወኢ ታምልክሙ) አትስገድላቸው ፡ አታምልካቸውም የሚለውን የአምላክን ትእዛዝ ተላልፋችኋል ማለት እውነቱን ከሐሰት ፡ ሃይማኖቱን ከክህደት ዕውቀቱን ከድንቍርና ጋራ ማማታት መሆኑን አንባቢዎች ሁሉ ይገንዘቡት ።

ምክንያቱም ፡ ለቅድስት ድንግል እመቤታችን ፡ ለጻድቃን ለሰማዕት ፡ ለሐዋርያት ለመላእክት የአክብሮት ስግደት ስናቀርብ ፡ የአምልኮት ስግደትን ለእግዚአብሔር ብቻ ከማቅረብ ያልተገታን መሆናችንን ነው ።

## ፯ኛ ምዕራፍ ።

## ስለ መጽሐፈ ሄኖክ ።

ለአዳም ሰበተኛ ትውልድ የሆነ ሄኖክ ፡ ነቢየ እግዚአብሔር መሆኑ በብሉዩና በሐዲስ መጻሕፍት ተረጋግጧል ።

እግዚአብሔርን ያገለገለ ደግ ሰው ስለ መሆኑም ከዚህ ቀደም በአንደኛው መርሐ ምእመናን እንደ ገለጥነው አሪት ዘፍጥረት (ወአሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሔር ፡ ወኢተረክበ እስመ ከበቶ እግዚአብሔር) ሄኖክም አከሐዱን ከእግዚአብሔር ጋራ ስለ አደረገ አልተገኘም ። እግዚአብሔር ወስዶታልና ብሏል ። አሪ ዘፍ ም ፭ ቍ ፳፬ ።

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክትም (በተአምኖ ፈለሰ ሄኖክ ከመ ኢይርአዮ ለሞት ፡ ወኢተረክበ እስመ ከበቶ

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ። ወዘእንበለ ያፍልስ ሰማዕተ ከኖ ክመ አሥመሮ ለእግዚአብሔር "ወዘእንበለ ተእምኖሰ ኢይትከሀል ያሥምርዎ) ሄኖክ ሞትን እንዳያየው በሃይማኖት ከዚህ ዓለም ወጣ ፤ ለሞትም አልተገኘም ። እግዚአብሔር ሠውሮታልና ። ከዚህ ዓለም ሳያጠጣውም ፤ እግዚአብሔርን እንደገለገለው መሰከረለት ብሎ አስረድቷል ። ዕብ ም ፲፩ ቍ ፭—፮ ።

ሄኖክ ፤ ፍጹም ሃይማኖት ያለውና እግዚአብሔርን የገለገለ መሆኑ ከተመሰከረለት ፤ ቃሉን የሃይማኖታዊ ፤ ወይም የነቢየ እግዚአብሔር ቃል ነው ብለን (አክብረን) ልንቀበለው እንዴት አይገባም ?

ይህንን የምንልበት ምክንያት ፤ ሐዋርያው ደግሞ ሃይማኖቱን፣እግዚአብሔርን ማገልገሉን ከዚህ በላይ እንደ ተነገረው ቃል የመሰከረለት ሲሆን ፤ ከቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የራቀ አንድ ተቃዋሚ ፤ የሄኖክን መጽሐፍ መቀበል አይገባም እያለ ያወራል ።

ሄኖክ ፤ ደግነቱ እንዲህ በብዙ ወገን የተመሰከረለት የእግዚአብሐር ወዳጅ ሆኖ ሳለ ፤ አንድ መናፍቅ መጽሐፉን መቀበል አይገባም ብሏል እያልን ልናደንቅ አይገባም። እሱ ግን፤ ሐዋርያው ይሁዳ በከመ ተነበየ ሄኖክ ብሎ ሲመሰክርለት እንዲህ ካለ ፤ ሄኖክ ነቢየ ጽድቅ ነው ወይስ ነቢየ ሐሰት ፤ ነቢየ ጣዖት ነው፤ ወይስ ነቢየ እግዚአብሔር ብለን ስንጠይቀው ኀፍረትን ለብሶ ይሔዳል ።



በሃይማኖታዊነታቸው አርባ ቀን መንክራዊ ብርሃን የወረደላቸው ያዒ ዘርአ ያዕቆብ ንግግር ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጻድቁ አፄ ዘርአ ያዕቆብ ብሉያትንና ሐዲሳትን የተማሩ ከመሆናቸው በላይ፣ የበቁ ስለ ነበሩ ፤ በደብረ ብርሃን ሳሉ በአዘጋጁት መጽሐፈ ብርሃን ስለ መጽሐፈ ሄኖክ እንዲህ የሚል ቃል ሰጥተዋል ።

«የሄኖክን መጽሐፍ አባቶቻችን ሐዋርያት (በከመ ተነበየ ሄኖክ በእንቲአሆሙ ዘውእቱ ሳብዕ እም አዳም) የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነ ሄኖክ ስለእርሳቸው ትንቢት እንደ ተናገረ ብለው ምስክር አድርገው ስለ አጸኑት እንቀበለዋለን ።

አሪትም ፤ ሄኖክ እግዚአብሔርን ስለአገለገለው አልተገኘም ፡ እግዚአብሔር ሠውሮታልና ትላለች ።

እግዚአብሔርም በመጽሐፈ ኩፋሌ ስለእርሱ ለሙሴ እንዲህ ብሎታል ።

እርሱ ሄኖክ አስቀድሞ ማስረጃ የጻፈ ፤ ምስክርነቱንም ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ይሰማ ነው ።

የኢዮቤልዩን ሱባዔ ፡ የዓመታትን ቀኖች ፤ ወሮችንም የተናገረ ፤ የዓመታትንም ሰንበታት የሠራ እሱ ነው ።

ዳግመኛ ፡ ልዑል እግዚአብሔር የሄኖክን ነገር ሲያጸድቅ ፤ (ሲያረጋግጥ) በመጽሐፈ ኩፋሌ ለሙሴ እንዲህ ብሎታል ።

www.ethiopianorthodox.org

አንተ ሰው ሄኖክ እንደተናገረው የሣስት መቶ ስሳ አራት ቀኖችን ቍጥር እንዲጠብቁ የእስራኤልን ልጆች አዘዛቸው ። ይኸውም ፍጹም ዓመት ይኾናል ።

ቅዱስ ጳውሎስም ፤ ሞትን እንዳያየው በሃይማኖቱ አሳርጎታል ብሏል ።

አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከዚህ በላይ የተነገረውን ቃለ ሐተታ ከሰጡ በኋላ፡ ሐዋርያት በሐዋርያው በይሁዳ መጽሐፈ መል እክት ምስክር ያደረጉትን ፤ እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮ በመ ጽሐፈ ኩፋሌ የመሰከረለትን የሄኖክን መጽሐፍ አልቀበ ለውም የምትል አንተ ሰው እስኪ ተመልከት ።

(እፎኑ ይትከሀለከ ታእምር ዑደተ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት ፤ ምልአተ ብርሃን ወሐፃፄሁ ፤ ወሥርቀተ ዓመታት ዘእንበለ መጽሐፈ ሄኖክ) የሄኖክን መጽሐፍ ሳትቀበል የፀሐይን ፤ የጨረቃን የከዋክብትንም አ፱.፱.ር የብርሃናትን አመላልና ኣጐዳደል ፤ የዓመታትንም ብተት ለማወቅ እንዴት ይቻልኻል ።

ሐዋርያትም በዲድስቅልያ የሄኖክን መጽሐፍ ከሙሴ ከዳዊትና ከኢሳይያስ መጽሐፍ ጋራ አስተካክለውታል ።

ስለዚህ ፤ ሐዋርያት ለምስክርነት እንደ ተቀበሉት እኛም እንቀበለዋለን ፤ እንወደዋለንም ብለዋል ።

እኛም ፤ ሄኖክ በትውልድ አቈጣጠር የእግዚአብሔር ወዳጆች ከሆኑአበው ከነሄኖስ ከነመላልኤል ፤ ከነያሬድ



ከነሚም ጋራ የተቈጠረ ደገኛ ሰው ስለ ኾነ ፤ ከሃይማኖት ውጪ አድርገን ልንመለከተው አይገባም ።

ሆኖም ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን የሄኖክን መጽሐፍ አክብራ ለምስክርነት የተቀበለች በትን ምክንያት አፄ ዘርአ ያዕቆብ ከዚህ በበለጠ ኀይለ ቃል አስረድተዋል ።

በአንደኛው መርሐ ምእመናንም እንደ ተገለጠ ፤ ጻድ ቃን ሰማዕታት ኢያማልዱም ያሉ መናፍቃን በእግዚአብሐር ተአምራትና በሊቃውንት ቃል መረታታቸው ስለታወቀ ፤ ለሊቃውንት አፍም ፤ ጥበብም እኽናቸዋለሁ ላለ ሊቀ ማኅበር ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ይግባው ።

www.ethiopianorthodox.org

የቋንጣ መስቀያ እንደምን ይባላል ።
የሰማዕታትና የጻድቃን አበው ።
እንደ ምን ይከዳል ማማለዳቸው ።
ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ ሕያው ።
የጻፈውን ነገር ባለማሰብ ነው ።
ባንዱ ጻድቅ ሰው ስም አንዱን ጻድቅ ሰው ።
አክብሮ በቤቱ የተቀበለው ።
እኔ እሰጠዋለሁ አይቀርም ዋጋው ።
በተማሪዮ ስም በተወደደው ።
ለአንዱ ጽዋ ውኃ የሚያጠጣ ሰው ።
አለው ብዙ ዋጋ እኔ እምሰጠው ።
እንድናከብራቸው እንዲህ ብሎ ጽፎ ።
ያስከበራቸውን ዐዋጅ አስለፍፎ ።
ቅዱሳንን መንቀፍ ይህንን ቃል አልፎ ።
የጻፈ ሰው ቢኖር ቅዱሳንን ዘልፎ ።
ገሃነም ነው ቤቱ ሥቃይ ተገናጽፎ ።
በምድርም ይኖራል መከራን አትርፎ
የጥምቀት ጸጋውን ልጅነቱን ገፎ ።
በወንጌል ያለውን ቃልኪዳኑን ገድፎ ።
ድርሰት ጽፎልና ቅዱሳንን ነቅፎ ።
ራሱን እያለ ሰድቦ ተጸይፎ ፤
እኛስ እንወለዳለን ቅዱሳኖችን ።



ደግሞም እናምናለን እንዲያማልዱን ፤
በቃል ኪዳናቸው እንደሚረዱን ፤
ግዳጅ እንደትፈጽም ጸሎተ ጻድቃን ፤
ቅዱስ ያዕቆብም ጽፎ አስታወቀን ፤
እንዲህ ስናስረዳው ምሥጢሩን ገልጠን ፤
አያማልዱንም ብሎ የሚለን ፤
ከቶም አላመነም ቃለ ወንጌልን ፤
አጥብቆ ይሠረው የጴጥሮስ ሥልጣን ፤
ከክርስቶስ ጉባኤ የራቀ እንዲሆን ፤

---

የመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር የሊቀ ጠበብት ተክለ
ሚካኤል በልሁ

፩ኛ መወድስ (ቅኔ ።)

መኑመ ይክል ነቢበ ምሳሌ ፤ ዘይመስላ ለጽዮን ወላዲተ ቃል ቅዱስ ። ወበወሊዶታ እሳተ አምሳለ ጸጠስ፤ አንክሮሰ ናንክር በጉባኤነ ።

ድንግል ድኅረ ወሊደቶ ለሕያው ክርስቶስ ። እስመ ተቀደሰ በመንፈስ ፤ ኵሉ ዓለም ጸሐፊ ኂሩታ ቀለመ ፈውስ ።

ለ ዓ ለ ም ።

ያወዕእዚ ሠርፀ አዕጓኖ ብዝኀ ኂሩታ በለስ ። ወዘ ኢየአምን ፤ በኂሩታ እመጽሐፈ ሕይወት ይደመሰስ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ትብል ጎይልየ ሊተ ወሊዶ ማስያስ ርእስ ፡ ወድ ፈትሖ ፍትሐ ኵሉ እንተ ወለዶ ማስያስ ።

## ፬ኛ መወድስ ።

መደልዋኒ ቅድም ወድኅር በሀላዌክሙ ፡ ኢያንበብ ክሙ ወንጌለ ዘተጽሕፈ ለዓለም ። ወእንተ ይቤ ወን ጌል ኢሰማዕክሙ እምቅድም ። እንዘ ይብል አክብር አበ ዚአከ ፡ ወእመከ እለ ወለዱከ በሥጋ ወደም ። እንዘ ከመገዘፍ ይጌርም ፡ እሬት ኢንክል አክበሮት እምነ ማር ያም ። አምጣነ ይእቲ ቃድሳን ፡ እሞት ኃጢአት ሕሱም ። በይነ ዘወለደት መድኃኔተ ለቢዘ ሕዝበ ዮም ወትማልም ። ወዘወለዶ ቃለ እንዘ በግብረ መዕምም ይቀጠቅጥ ጸላኢሃ በብትረ መዓቱ ወበቀስታም ።

## ፭ኛ መወድስ ።

ሰንቄ በሕርየ ጽድቅ ስምኪ በኢትዮጵያ ፡ ኵለሄ ያበርህ ለዘበወልድኪ ተመሰለ ። ጽላሎተ ሞቶ መሪር እስ ከነሰሰለ ። በኀይለ ሥላሴ ወበስልዮስ ብርሃናተ አምጣነ ርኢነ ንኪልአነ ኃይለ ። ማርያም ዘተመሰልኪ ርግበ ቤተ ኖኅ ዘአምጽአት እምድኅረ ማየ አይኅ ቈጽለ ። መልእክቲ ገዘረ ስምኪ ኢትዮጵያን ኄለ ፡ እምይእቲ ኢትዮጵያ አሰስሎተ ፀር አምጣነ ከሀለ ። በኀይለ ሥላሴ ንጉሥ ዘተቀጸለ አክሊለ ። ወለንጉሥ ጽድቅ ኀይለ ሥላሴ ይዌ ስክ መዋዕለ ።



## ፮ኛ መወድስ ።

እግዚአብሔር ይሴብሑ በኢትዮጵያ ፡ ወይትባረክ ዘልፈ እግዚአብሔር አምላክነ ። በኢትዮጵያ ሀገር አም ጣነ እንሥአ ለነ፡ ቀርነ መድኃኒት ኃይለ ሥላሴ ።

ወበስልዮስ ዕምደ ሃይማኖት ተፈነወ ለነ ። በመጽ ሐፈ አበው ከመ ሰማዕነ ፡ አርአየ ሢመቱ ሐዲስ በኀይለ ሥላሴ እስመ ርኢነ ።

## ሰዓለም ።

በይእቲሂ ኢትዮጵያ ሀገረ ኵልነ ። እምርት ለፍጻሜ ሢመተ በስልዮስ በዓልነ ። ወበቡራኬሁ ሐዲስ እመ በረከነ ። ንነሥእ በረከተ እንዘ ናስተራትዕ ጉብኤነ ።

---

## ከእለታ ይትባረክ መርሻ ፩ኛ መወድስ

ዘመዱ እንስሳ ይትረአይ በግዕዘ እንስሳ ፡ ወዘመዱ
ሰብእ ይንግእ ግዕዘ ሰብእ ዘኢያርምሞ ።
እመኒ ለሰብእ ውኑዘ አእምሮ አስጠሞ ።
ሰብእ ዘአእምሮ ፡ ፈለጠ በግዕዘ አእምሮ አበሁ ወእሞ ።
ዘመዱ እንስሳሰ ኢፈለጠ ፡ ቤተ ክርስቲያን እመ ወአበ
ተሳልሞ ።
ፈረስሂ ጽንዐ ሕግነ ፡ ዘለዕፀ ሐሜት ገዘሞ ።
እምከመ ዐርትአ ፍናዊሁ ልጓመ ዘለፉ ኢያቀውሞ ።
አኮኑ ለኃጕል ፈረሰ ፈርዖን ቀደሞ ።
ከናፍረ ጥበብ ሊቃውንተ መጠነ ጎዳጠ ኢያሕመሞ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፬ኛ መወድስ ።

እምዓለም ዓለመ በከመ ተብህለ ፡ ዘኢ.ሀለም ዕዋል ይሜንን ወሬዶኑ ።
ናሁ ተከሥተ ወአስተርአየ ኅቤነ ።
እስመ ከመ ያጽድቅ ዘተነግረ ፡ ጕልያድ ነጻየ አእምሮ ይሜንን ጻድቃነ ።
ዘይመልዕበበያተ፡ጸሎተ·ብዕሎሙ መዘግብተ እከይ ኃጥአን።

## ለ ዓ ለ ም ።

በሕቱ ኢይትፈታሕ ለእመ ይሜንን ዕብነ ።
ከመ ዕብን ፀላኢሁ አኮኑ አጠየቀነ ።
ኃይለ ወልደ ዕሚይ ዘለብሰ ህየንተ ልብሰ ብርት አሚነ ።
ለእለ ሐነጸ ተዋሕዶ ቤተ ጽድቅ ልቡናነ ።

## ፭ኛ መወድስ ።

በ መስቀል ህየንተ መስቀል ከመ በአይሁድ አይሁድ ወከመ በማኒ ዘማኒ ።
እስመ ኢመበ በእግር እንተ ዕሌኒ ዕሌኒ ።
በ ቈስጠንጢኖስ ፡ እንተ በኮላሄ መንግሥቱ ሰፋኒ ።
እምገዘ ቃለ ተነግሮ አሰማደ መስቀል ይግነዩ ለዘዓለመ ያገኒ።
እንከሰ ሰፀ መስቀል ዓለመ ዓለም ኮናኒ ።
ልሳን ሐመልሚላዊ ኢ.ኮንኖ መስቀል ኢ.ያመክኒ ።
ሐመልሚላዊ ልሳነ እስመ ከመ አግብርት ይቀኒ ።



መስቀል ሐዋርያ ሠሪዓ ቤተ ሐዋን ዘያሚኒ ።

## ጉባዔ ቃና ።

ለዘበርሀተ ርግብ አምሳለ ድንግል ብርሀት ።
ገበዋቲሃ ጻድቃን ወሐመልማለ ወርቅ ገነት ።

---

## የሊቀ መዘምራን አክሊሉ ገብረ ኪሮስ ዘበአታ (መታሰቢያ ቤት) መወድስ ቅኔ ።

ኃይለ ተናግሮ ይትረከብ እም አፈ ጳላኢ ። ሥርወ አፈ ንስጥሮስ ይምትር በሰይፈ ቃሉ መላጺ ። እስመ ኅይለ ንባብ ነሥአ እመንፈስ ቅዱስ ሐዋጺ ። እምድኅረ ሆኮ አፈ ጳላኢ ።
ቄርሎስ ዐምደ ሃይማኖት ዘበጽድቅ ሠራዒ ። በኃይለ ቃሉ እስከ ፀፀወ ማዕያ ንስጥሮስ አፈ ሙባአ ክህደት ረዋጺ ።

## ለ ዓ ለ ም ።

ተውህቦሂ ለጉባኤነ አፈ ሃይማኖት ገሣጺ ።ለቤተ ክርስቲያን እስከ ይቤላ እም ዘነሠቱኪ ትትሐነጺ ።
አኮኑ ኬድዎ በእግረ ትዕቢት አዕቃጺ ለተቃውሞ አፈ ኀጥእ ፣ ወለተዘልፎ አፈ ዐማፂ ።

---

## የሐረር መካነ ሥላሴ ቅኔ መምህር የሊቀ ጠበብት ማእምር አለማሁ መወድስ ።

አሌ ለክሙ ደቂቀ ውላጤ ለእሳተ ንስጥሮስ ክህድ እለ ድልዋን በሐሰት ። እስመ ውስጥክሙ ከነ ምሉእ ዐመፃ

ከህይወት ። ወእንዘ ሀሎ ውስተ ቤትነ ።

ቄርሎስ እንተ ይሴለዮ ሃይማኖት ጉብስት ፡ ትሴለዩ በዐ መዓ መብልዐ ንስዋርስ ከህዪ እንተ ኢይከውን ለሕይወት።

## ሰ ዓ ለ ም ።

ቅድመሂ እምከርሠ እም ተፈጥሮትክሙ ምንት ። እስመ ገቢረ ጽድቅ ምረርክሙ ወመዐርክሙ ኃጢአት ።

በሕቱ ንስሕል ነገደ ሴዊ ከህናት ። ከመ ንኩን ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ፍቅረ እግዚአት ።

---

## ክእለፍ አርአዩ ተክለ ሥላሴ ።

## መወድስ ።

ደብረ ሊባኖስ እምከ ወላዲተ ንጽሕ ፡ ስምዐ ጽድቅ ትኩንከ ለሰለተ መርሕከ ጽድቅና ።

ኩሉሓ ሃይማኖት እንተ በከመ ወልዱ ለዮና ።

እግዚእ አርምዮስ እስመ ይቤ ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ ዘፈተውኩ ሥና ።

ወአስተናደፍኩ መሠረታ ለእንተ ፈጸማ ጳውሎስ መሠረተ ኤልያስ ድንግልና ።

## ሰ ዓ ለ ም ።

ባስልዮስሂ ዘትሰቀይ በዘሊሳይያስ ፍና ።

ሀሊብ ትምህርት ሃይማኖት ወጠለ ገዳም ምንኩስና ።



ዘበሕጉ ይትጋደል እስመ ይከውኖ ምግባር ።

አዕሩገ ወንጌል እንዘ ይብሉከ ዘበአርያም ሀገሪና ።

## መወድስ ።

ዐፅደ ወይና ለማብጽ ሕግ አጺስና እምግብጽ እና ሰስከ ወተከልከ ሥረዊሃ ።

ከመ ትምላእ ምድረ አዕጹቂሃ ።

እክኑ ባሰልዮስ ኢትፈቅድ ሠርጐ ሰማያት ዐሐየ ወወርኀ ።

ኃይለ ሥላሴ ዘይቤለከ ነየ እምከ ኢትዮጵያ ለሊሃ ።

## ሰ ዓ ለ ም ።

ባስልዮስሂ ነቅዐ ምሥጢር ለጥበበ ገድል አበሃ ። በትረ ሃይማኖትከ ዘትሀብ ፍሬሃ በበጊዜሃ ። ወለፍኖተ ንጽሕ ገድል ከመትኩነነ መርሐ ለጥበብ ተዋሕዶ ባስልዮስ ቀዳሚሃ ።

## መወድስ ።

ሃይማኖት ጥይቅት ለዘይሴፈዋ ፤ ወለዘኢይሴፎ ባቲ ዐስበ ጌጋዩ ለበለዓም ። እስመ ዲበ ርእሱ ይትጋባእ ትን ታገ አፍሐም ።

ወለሃይማኖት ዕፀ ምንታዌ ድኩም ዐጽቃ ወቄጽላ ልምሉም ።

ኅጡተ ሰናፔሴ ተዋሕዶ ታሕተ አዕጹቂሃ ታጼልል ዘመደ አዕዋፍ ዘምድያም ።

እመሰ ሃይማኖትነ አሠረ ምንታዌ ተቅራም ። አይቴኑ ስብሐ ሥርናይ ፤ ወአይቴ መሥዋዕተ ደም ። ወእመ እሉ ኢነሥኡ ትድምርተ ሥጋ ወዐፅም ። ገነ ውተ አማልክት እምኀሠሡ ተረፈ አሪት መሥዋዕተ ላሕም ።

ይቀጥላል ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yohannes
0911360113
www.ethiopianorthodox.org